የአየርላንድ ዜግነት መስጠትና ፍልሰት አገልግሎት

አለማቀፍ ጥበቃ ቢሮ

# የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ መረጃ መጸሀፍ

**እባክዎን የአለም አቀፍ ጥበቃ መጠይቁን ከመሙላቶት በፊት በዚህ መጸሀፍ ላይ ያለውን መረጃ በሙላ ያንብቡ**

## የዚህ መጸሀፍ (ቡክሌት) ተግባር

ይህ የመረጃ መጸሀፍ በአየርላን ስላለው አለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻው አካሄድ እንዲረዱ ያግዞታል፡ ፡ እንዲሁም መብቶችና ግዴታዎችዎትን የሚያብራራና የእርሶ ማመልከቻ፣ ምርመራና ምክር/ውሳኔ ሂደት ከማን ጋር ግንኙነት እንዳለው ያሳያል፡፡ እንዲሁም ይህ መጸሀፍ በሌሎች ምክንያቶች ላይ ለመቆየት ፈቃድ ያለውን እሺታ በተመለከተ መረጃ ይሰጣል፡፡

## ጠቃሚ ማስታወሻዎች

ይህንን የመረጃ መጸሀፍ በማስቀመጥ ማመልከቻዎት መሄድ ሲጀምር እንደማጣቀሻነት ይጠቀሙበታል፡ ፡

አለም አቀፍ ማመልከቻዎትን በሚያስገቡ ግዜ፣ በህጋዊ ሂደት ውስጥ ገብተዋል ማለት ነው፡፡ በማመልከቻ፣ ምርመራና ምክር/ውሳኔ ሂደት ላይ የሚያቀርቡት ሰነድና መረጃ የሂደቱ ማእከል ነው፡፡ ስለዚህ፣ የሚከተሉትን መረጃዎች በሙላ ማንበብ አስፈላጊና ካስፈለገም የሕግ ምክር በመሻት ለማመልከቻዎት የሚረዳ ቦታ ላይ ይደርሳሉ ማለት ነው፡፡ ከአለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ (አይፒኦ) ጋር በትብብር መስራት ይኖርቦታል፡፡ ይህን ሳይደረግ ከቀረ ግን፣ በማመልከቻዎት ውጤት መሰረት በከባድ ሁኔታ በህግ መጠየቅ ሊከተል ይችላል፡፡

የአለም አቀፍ ጥበቃን ማመልከቻ ምርመራና ውሳኔ እንዲሁም የመቆየት ፈቃድና በአየርላንድ ከቤተሰብ ጋር የማገናኘቱ/ማቀላቀሉ ሂደት የሚያስተዳድረው ህግ የተመሰረተው በአለም አቀፍ ጥበቃ አዋጅ 2015 (የ 2015 አዋጅ) እና በሕጉ ስር ባሉ ትእዛዞችና ደንቦች መሰረት ነው፡፡ እነዚህን ሕጎች በሙላ በ www.inis.gov.ie እና በ www.ipo.gov.ie ድረገጾች ላይ ማግኘት ይችላሉ፡፡

ይህ መጸሀፍ የሚያገለግለው ለመረጃና መመሪያ ብቻ ነው፡፡ ይህ መጸሀፍ ለህግ ምክር የማያገለግልና ለአለም አቀፍ ጥበቃ አዋጅ 2015 ምንም አይነት ትርጉም የማይሰጥ ነው፡፡ አዋጅ 2015 ጉዳዮት ላይ ተጽእኖ ካለው እንዲሁም በዚህ ላይ የበለጠ መረጃ ለማግኘት የሕግ ምክር ያግኙ፡፡

የመጸሀፉ ይዘት ትክክለኛ እንዲሆን ያላሰለሰ ጥረት ተደርጓል፣ በዚህ ላይ ስህተት ወይም የጠፋ ነገር ካለ ሀላፊነት ሊኖር አይችልም፡፡ ከዚህም በላይ፣ በዚህ መጸሀፍ ላይ ያለው ይዘት በፍትህና እኩልነት ሚኒስቴር (‹ሚኒስቴሩ›) ወይም በማንኛውም አካል፣ ይህም የአለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ባደረቦችና ሰራተኞችን ጨምሮ፣ በሕግ ከተቀመጠው ባሻገር ሕጉን ተንተርሶ የሚወክል ወይም ቃል የሚገባ አይደለም፡፡

አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ
አየርላንድ ዜግነት የመስጠትና ፍልሰት አገልግሎት

ጥር 2017

**ማውጫ**


**ክፍል 1 አለማቀፍ ጥበቃ ምንድነው፣ እንዴትስ ለሱ ማመልከት ይቻላል?**

*1.1 አለማቀፍ ጥበቃ ምንድነው?*
*1.2 ለአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከት የሚችለው ማነው?*
*1.3 ለአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቴ ከሁኔታዬ አንጻር ለኔ ትክክለኛ እርምጃ ነው?*
*1.4 የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዬን የማስገባው የት ነው?*
*1.5 የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዬን የሚመለከተው ማነው?*
*1.6 የመቆየቱ ፈቃድ ምንድነው፣ ለዚህም እንዴት ማመልከት እችላለሁ?*
*1.7 ከቤተሰብ ጋር መቀላቀል ምንድነው?*

**ክፍል 2 ጠቃሚ ቃላት**

*2.1 አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ (አይፒኦ) ምንድነው?*
*2.2 የአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ልዩ ችሎት (አይፒኤቲ) ምንድነው?*
*2.3 ሚኒስቴሩ ማነው?*
*2.4 እንደ ስደተኛ የሚቆጠረው ማነው?*
*2.5 ለንዑስ ጥበቃ ብቁ የሚሆነው ማነው?*
*2.6 ከፍተኛ ጉዳት ምንድነው?*
*2.7 ወደ መጡበት የመመለስ ክልከላ ምንድነው?*
*2.8 ከአለም አቀፍ ጥበቃ የሚገለለው ማነው?*
*2.9 ኢዩአርኦዲኤሲ ምንድነው?*
*2.10 የጋራ የጉዞ ቦታ ክልል ምንድነው?*

**ክፍል 3 የአለም አቀፍ ጥበቃ ሂደት**

*3.1 ለአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዬን ካስገባሁ በኋላ ምን መጠበቅ እችላለሁ?*
*3.2 የማመልከቱ ሂደት የመጀመሪያው እርምጃ ምንድነው?*
*3.3 ማመልከቻው ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችለው እንዴት ነው?*
*3.4 ለአለም አቀፍ ጥበቃ ቀድሜ ባመለከትኩት ላይ ውሳኔ ደርሶኛል፣ ሌላ ማመልከቻ ማስገባት እችላለሁ (ተከታይ ማመልከቻ)?*
*3.5 የመጀመሪያው ቃለ መጠይቅ ምንድነው?*
*3.6 የጣት አሻራና ሌሎች የባዮሜትሪክ መረጃዎችን መውሰድ አለብኝ?*
*3.7 ከአለም አቀፍ ጥበቃ ሂደት የጽሁፍ መረጃ ይደርሰኛል?*
*3.8 ለአለም አቀፍ ጥበቃ ሳመለክት ምን ይዤ መምጣት አለብኝ?*
*3.9 የግዜአዊ መኖሪያ ሰርተፍኬት (ቲአርሲ) ምንድነው፣ መቼስ ነው የምቀበለው?*
*3.10 የአካል ጉዳት ቢኖርብኝ ወይም ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልገኝ ከሆነ ምን ይሆናል?*
*3.11 በጥበቃ ስር ወይም በእስር እያለሁ ለአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከት እችላለሁ?*
*3.12 ለአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካች የሚታሰርበት ሁኔታ ምንድነው?*
*3.13 በእኔ ላይ ጥገኛ ሆነው የሚኖሩ ከ18 ዓመት በታች ካሉስ?*
*3.14 የህግ ምክር ከየት አገኛለሁ?*
*3.15 ለአለም አቀፍ ጥበቃ ያስገባሁትን ማመልከቻ ማቆም እችላለሁ?*

## ክፍል 4 ቃለ መጠይቅ እና ምርመራ

*4.1 በአለም አቀፍ ጥበቃ ቃለመጠይቁ ላይ ምን ልጠብቅ እችላለሁ?*
*4.2 የሚረዳኝን ማንኛውንም ሰው ይዤ ወደ አለም አቀፍ ጥበቃ ቃለመጠይቁ መምጣት እችላለሁ?*
*4.3 በቃለመጠይቁ ላይ መገኘት ካልቻልኩ ወይም ከቀረሁ ምን ይሆናል?*
*4.4 በማመልከቻው ሂደት ላይ መተባበር ግዴታ አለብኝ? ሳልተባበር መቅረቴ ምን ያስከትላል?*
*4.5 የግል ቃለመጠይቁን ጨምሮ የምርመራው ዋና ሂደት ምንድን ነው?*
*4.6 ከቃለመጠይቁ በኋላ ምን ይመጣል?*
*4.7 የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ላይ ሊያመጣቸው የሚችሉ ውጤቶች ምንድን ናቸው?*
*4.8 ለአለም አቀፍ ጥበቃ ባቀረብኩት ማመልከቻ ላይ የውሳኔ ሃሳብ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ካልደረሰኝ ምን ይፈጠራል?*

## ክፍል 5 ይግባኝና የአለም አቀፍ ጥበቃ

*5.1 እኔ አለም አቀፍ ጥበቃ እንዳይሰጠኝ በሚቀርቡት እና በሌሎች የውሳኔ ሃሳቦች ላይ ይግባኝ የመጠየቅ መብት አለኝ?*
*5.2 ይግባኝ እንዴት ነው የማቀርበው?*
*5.3 ይግባኝ ለማቅረብ የጊዜ ገደቡ ምን ያህል ነው?*
*5.4 ለይግባኙ የህግ ተወካይ የማቅረብ መብት አለኝ?*
*5.5 ይግባኝ በምን ያህል ፍጥነት ሊታይ ይችላል?*
*5.6 ስለ ይግባኝ ሂደት የበለጠ መረጃ ከየት ላገኝ እችላለሁ?*

## ክፍል 6 የስደተኛነት ወይም ንዑስ ጥበቃ ማረጋገጫ

*6.1 የውሳኔ ሃሳብ ከተቀበልኩ በኋላ ምን ይከሰታል?*

## ክፍል 7 የአለም አቀፍ ጥበቃ ካገኙ የሚኖሮት መብት

*7.1 የአለም አቀፍ ጥበቃ ካገኘው የሚኖሩኝ መብቶች ምንድን ናቸው?*

## ክፍል 8 በአለም አቀፍ ጥበቃ ሂደት ውስጥ ያሎት መብቶችና ግዴታዎች

*8.1 በአለም አቀፍ ጥበቃ ሂደት ውስጥ ያሉኝ መብቶችና ግዴታዎች ምንድን ናቸው?*
*8.2 በአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ሂደት ውስጥ ያሉ ግዴታዎች ምንድን ናቸው?*

## ክፍል 9 አብሯቸው ሰው የሌለ ሕጻናት

*9.1 እኔ አብሮኝ ሰው እንደሌለኝ ህጻን ሆኜ የአለም አቀፍ ጥበቃ ባመለከት ምን ይፈጠራል?*
*9.2 ቱስላ - የህጻናትና ቤተሰብ ኤጀንሲ ለእኔ የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ካስገባልኝ የሚኖረው ሂደት ምንድን ነው?*
*9.3 ከ18 አመት በታች የሆነ ህጻን ወደ ህግ ድጋፍ ቦርድ ለመምራት ያለው ሂደት ምንድን ነው?*

**ክፍል 10 ኢዩ (አውሮፓ ህብረት) ደብሊን ደንብ**

*10.1 ኢዩ (አውሮፓ ህብረት) ደብሊን ደንብ*

**ክፍል 11 በፈቃደኝነት የመመለስ አማራጮች**

*11.1 መጣሁበት ሀገር/ቀድመው እኖርበት ወደ ነበረው ሀገር በፍቃደኝነት የመመለስ አማራጭ አለኝ?*

**ክፍል 12 ሌላ መረጃ**

*12.1 ለአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ቅድሚያ ለመስጠት ያሉ ሂደቶች ምንድን ናቸው?*

*12.2 ለአለም አቀፍ ጥበቃ ጽ/ቤት ያቀረብኩት መረጃ ምን ይደረጋል?*

**ክፍል 13 የመቆየት ፈቃድ**

*13.1 የመቆየት ፈቃድ ለማግኘት እዴት ነው የማመለከተው?*
*13.2 በስቴቱ (አየርላንድ) ውስጥ ለመቆየት ወይም ላለመቆየት ሚኒስቴሩ ፈቃድ ለመስጠት ወይም ለመከልከል ምን አይነት መረጃ አስፈላጊ ነው?*
*13.3 የመቆየት ፈቃድ ከተከለከልኩኝ ምን ይፈጠራል?*
*13.4 የመቆየት ፈቃድ ከተሰጠኝ ምን ይፈጠራል?*
*13.5 የመቆየት ፈቃድ ክልከላ እንዴት «በድጋሚ ይታያል»?*
*13.6 የመቆየት ፈቃድ ቢሰጠኝ እና በአይፒኦ በእኔ የጥበቃ ማመልከቻ ላይ በተሰጠው የውሣኔ ሀሳብ ላይ ለአይፒኤቲ ይግባኝ ብል ምን ይፈጠራል?*
*13.7 ጉዳዩ በድጋሚ ከታየ በኋላ ፈቃድ ከተከለከልኩ ምን ይፈጠራል?*

**ክፍል 14 የቤተሰብ መቀላቀል**

*14.1 የቤተሰብ ቅልቅል/እንደገና መገናኘት ምንድን ነው?*
*14.2 የጊዜ ገደብ ይኖራል?*
*14.3 የቤተሰብ አባል ማን ነው?*
*14.4 በአለማቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ቅፅ እና መጠይቅ ውስጥ ምን ምን መረጃ ማካተት ይኖርብኛል?*
*14.5 ለቤተሰብ ቅልቅል ማመልከቻ የማቀርበው እንዴት ነው?*

**ክፍል 15 መኖሪያዎት**

*15.1 የቅበላ/ የመኖሪያ ቦታ መረጃ*

**ቅጥያ - የማግኛ ዝርዝሮች**

## ክፍል 1
## አለማቀፍ ጥበቃ ምንድነው፣ እንዴትስ ለሱ ማመልከት ይቻላል?

### 1.1 አለማቀፍ ጥበቃ ምንድነው?

1.1.1 በአለም አቀፍ የጥበቃ አዋጅ 2015 የተሸፈኑ ሁለት አይነት አለም አቀፍ ጥበቃዎች አሉ፣ እነሱም የስደተኞች ሁናቴና ንዑስ ጥበቃ ናቸው፡፡

**የስደተኞች ሁኔታ**

1.1.2 እንደ *ስደተኛ* ለመቆጠር፣ መሰረት ባለው በነዚህ ምክንያቶች የጥቃት ስጋት ያለበት ሰው መሆን ይኖርበታል፡-

(i) *ዘር፣*
(ii) *ሀይማኖት፣*
(iii) *ዜግነት፣*
(iv) *ፖለቲካዊ አመለካከት ወይም*
(v) *የተወሰነ የማህበራዊ ቡድን አባል መሆን፣*

*ዜግነት ካገኘበት/ካገኘችበት ከሀገሩ ወይም ከሀገሯ ውጭ ሆኖ/ሆና እና የማይችል ወይም፣ እነዚህ ስጋቶች ያሉበት፣ ከሀገሩ ጥበቃ ለማግኘት ፈቃደኛ ያልሆነ፣ ወይም ዜግነት የሌለው ሰው፣ በተመሳሳይ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የተነሳ ከሚኖርበት ሀገር ውጭ ያለ ወይም ያለች፣ ያልቻለ ወይም እነዚህ ስጋቶች ያሉበት፣ ለመመለስ ፈቃደኛ ያልሆነ፡፡*

**ንዑስ ጥበቃ ሁኔታዎች**

1.1.3 ስደተኛ ላለመባል ከወሰኑ፣ *ለንዑስ ጥበቃ መስፈርት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፣ ይህ የሚሆነው ወደ መጡበት ሀገር/ቀድመው የኖሩበት የነበረው ሀገር ቢመለሱ ከፍተኛ ጉዳት ሊደርስቦት እንሚችል የተጨበጠ መረጃ ካሎት ነው፡፡* ለበለጠ መረጃ **ክፍል 2.5.1** ይመልከቱ፡፡

### 1.2 ለአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከት የሚችለው ማነው?

1.2.1 እድሜው 18 አመትትና ከዛ በላይ እንዲሁም በግዛቱ (አየርላንድ) ዳርቻ ያለ ወይም በግዛቱ (አየርላንድ) ያለ ለአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከት ይችላል

(ሀ) እራሱን ወይም እራሷን ወክላ

(ለ) እድሜአቸው ከ 18 አመት በታች ለሆኑ ወይም በእሱ ወይም በሷ ሀላፊነት ስር ጥበቃ የሚደረግላትን ወክሎ፡፡

1.2.2 ይህ **በአንቀጽ 1.2.1** የተጠቀሰው የማመልከቻው ርእስ ነው፡፡
(ሀ) ተቀባይነት ለማግኘት (**አንቀጽ 3.3 ይመልከቱ**)፣ ወይም

(ለ) ተከታዩ ማመልከቻ በሚኒስቴሩ ተቀባይነት ካገኘ (**ክፍል 3.4** ይመልከቱ)፡፡

ጥገኛ ልጆችን በተመለከተ እባክዎን **ክፍል 3.13** ይመልከቱ፡፡

## 1.3 ለአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቴ ከሁኔታዬ አንጻር ለኔ ትክክለኛ እርምጃ ነው?

1.3.1 ወደ መጡበት ሀገር/ቀድመው የኖሩበት የነበረው ሀገር ላይ የመመለስ ስጋት ካሎት ብቻ ለአለም አቀፍ ጥበቃ ያመልከቱ፡፡

1.3.2 በስቴቱ (አየርላንድ) የመቆየት ሌላ ምክንያት ካሎት፣ እባክዎን በ www.inis.gov.ie ድረገጽ ላይ ያውን መረጃ ይመልከቱ፡፡

## 1.4 የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዬን የማስገባው የት ነው?

1.4.1 ማመልከቻዎትን <u>በአካል ተገኝተው</u> ለሚኒስቴሩ ማስገባት ይኖርቦታል፡፡ ይህንን በአየር ማረፊያ ወይም በአየርላንድ ባረፉበት ወደብ ወይም (ወደ ስቴቱ ከገቡ በኋላ) በቻሉት ፍጥነት ማድረግ ይኖርቦታል፣ ለማመልከት

**International Protection Office,**
**Irish Naturalisation and Immigration Service,**
**79-83 Lower Mount Street,**
**Dublin 2.**
**D02 ND99**

## 1.5 የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዬን የሚመለከተው ማነው?

1.5.1 ለአለም አቀፍ ጥበቃ በማመልከት፣ ሚኒስቴሩ ለስደተኛነት ሰነድ *ወይም* ለንዑስ ጥበቃ ሰነድ ብቁ መሆንዎትን እንዲመለከት ያደርገዋል፡፡

1.5.2 እንደ ነጠላ ማመልከቻ አካሄድ፣ የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዎት በአለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ባሉ የአለም አቀፍ ጥበቃ ባልደረቦች ተብለው በሚታወቁ በባለስልጣናት ይመረመራል፡፡ ይህ የአየርላንድ ዜግነት የመስጠትና ፍልሰት አገልግሎት ድርሻ ሆኖ በስሩ የፍትህና እኩልነት ክፍል አለው፡፡ በአይፒኦ ጋር ያሉ ሌሎች ሰዎችም በዚህ ሂደት ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡

## 1.6 የመቆየቱ ፈቃድ ምንድነው፣ ለዚህም እንዴት ማመልከት እችላለሁ?

1.6.1 አይፒኦ ምክረ ሀሳብ ለስደተኛ ሁናቴ ወይም ለንዑስ ጥበቃ አይሆኑም ካለ፣ ሚኒስቴሩ በሌላ ምክንያት (ለምሳሌ፣ በቤተሰብዎ ወይም በግል ሁኔታዎት ምክንያት) በስቴቱ (አየርላንድ) እንዲቆዩ ፈቃድ ሊሰጡትም ወይም ላይሰጡትም ይችላል፡፡ ይህ ስራ የሚከናወነው በአለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ነው፡፡ በአለም አቀፍ ጥበቃ መጠይቅ ላይ ጠቃሚ መረጃዎችን በተገቢው ቦታ ማስፈር ይኖርቦታል፡፡

እንዲሁም በሁኔታዎት ላይ ማንኛውም አይነት ለውጥ ካለ ውሳኔው እንዲሰጥ ወይም በስደተኛነት እንዲቆዩ የሚጠቅም ሊሆን ስለሚችል ለአይፒኦ ማሳወቅ ይኖርቦታል፡፡

ይህ **በክፍል 13** የበለጠ ተብራርቷል፡፡

## 1.7 ከቤተሰብ ጋር መቀላቀል ምንድነው?

17.1 ለስደተኛነት ወይም ለንኡስ ጥበቃ ሁኔታ እሺታን ካገኙ፣ ፈቃዱን ካገኙበት ጀምሮ በአንድ አመት ውስጥ፣ የተወሰኑት የቤተሰብዎ አባላት ወደ ስቴቱ (አየርላንድ) እንዲገቡ ፈቃድ ለማግኘት ለሚኒስቴሩ ሊያመለክቱ ይችላሉ፡፡ **ይህ የሚሆነው ለትዳር አጋር፣ ለተመሳሳይ ጾታ አጋር (ያገቡ ከሆነ ወይም የጥበቃ ማመልከቻውን ባስገቡበት ግዜ ከግለሰቡ ጋር ግንኙነት ጀምረው ከነበር)፣ ከ 18 አመት በታች ሆነው ያላገቡ ልጆችና፣ በትንሽነት ጥበቃ እሺታ ግዜ፣ ወላጆችንና ከ 18 አመት በታች ያሉ የአመልካች ወንድምና እህትን ያጠቃልላል፡፡**

1.7.2 ሚኒስቴሩ ማመልከቻውን በመመርመር፣ ግለሰቡ የቤተሰብ አባል ሆኖ በቤተሰብ መቀላቀል መስፈር የሚሸፈን ከሆነ፣ ግለሰቡ የነዋሪነት ፈቃድ ያገኛል፡፡

1.7.3 ሚኒስቴሩ በተለያዩ ምክንያቶች ይህም ከሕዝብ ደህንነት አንጻር፣ ከህዝብ ፖሊሲ ወይም ከህዝብ ማዘዣ ጨምሮ የቤተሰቡን አባል ከስደተኛነት ወይም ከንኡስ ጥበቃ ብቁነት ያስወድገደዋል ወይም ሊያስወግደው ይችላል፡፡

1.7.4 ለአለም አቀፍ ጥበቃ በሚያመለክቱ ግዜ ከቤተብ ጋር መልሶ ለማገናኘቱ (ማቀላቀሉ) ሂደት ሊጠቅም ስለሚችል ሁሉንም የቤተሰብ አባል ዝርዝር ማሳወቅ ይኖርቦታል ይህም ሚኒስቴሩ ለስደተኛነት ወይም ንኡስ ጥበቃ ሁናቴ ለሚሰጠው የመልሶ ማገናኘት ፈቃድ ያግዛል፡፡

1.7.5 ለበለጠ መረጃ **ክፍል 14** ይመልከቱ፡፡

## ክፍል 2
## ጠቃሚ ቃላት

### 2.1 አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ (አይፒኦ) ምንድነው?

2.1.1 አይፒኦ በአየርላንድ ዜግነት ሰጭና ፍልሰት አገልግሎት (አይኤንአይኤስ) ስር ያለ ቢሮ ነው፣ ሀላፊነቱም የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዎችን መመርመርና ማካሄድ ነው፡፡ የአይፒኦ ዋና የአለም አቀፍ ጥበቃ መኮንን ሹም እሱም ሲሆን የአለም አቀፍ ባልደረቦች ቡድንን የሚመራ ነው፡፡ የአይፖኦ መኮንን፣ በሚኒስትሩ ፋንታ፣ በስቴቱ (አየርላንድ) የመቆየት ፈቃድ ቢኖርም ባይኖርም ያልተሳኩ የአለም አቀፍ ማመልከቻዎችን ይመለከታል፡፡

### 2.2 የአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ልዩ ችሎት (አይፒኤቲ) ምንድነው?

2.2.1 አይፒኤቲ ሕጋዊ የሆነ ነጻ አካል ሲሆን የተቋቋመውም የአለም አቀፍ ይግባኖችን ለመወሰንና ሌሎች እንደዚ ያሉ ጉዳዮችን የአለም አቀፍ ጥበቃ ሕግ 2015 እና ሌሎች አስፈላጊ ህጎችን በመመርኮዝ ስራውን የሚያከናውን ነው፡፡

### 2.3 ሚኒስቴሩ ማነው?

2.3.1 ሚኒስቴሩ የፍትህና እኩልነት ሚኒስቴር ነው፡፡

### 2.4 እንደ ስደተኛ የሚቆጠረው ማነው?

2.4.1 እንደ *ስደተኛ* ለመቆጠር፣ መሰረት ባለው በነዚህ ምክንያቶች የመጎዳት ስጋት ያለበት ሰው መሆን ይኖርበታል፡-

(i) ዘር፣
(ii) ሀይማኖት፣
(iii) ዜግነት፣
(iv) ፖለቲካዊ አመለካከት ወይም
(v) የተወሰነ የማህበራዊ ቡድን አባል መሆን፣

ዜግነት ካገኘበት/ካገኘችበት ከሀገሩ ወይም ከሀገሯ ውጭ ሆኖ/ሆና እና የማይችል ወይም፣ እነዚህ ስጋቶች ያሉበት፣ ከሀገሩ ጥበቃ ለማግኘት ፈቃደኛ ያልሆነ፣ ወይም ዜግነት የሌለው ሰው፣ በተመሳሳይ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የተነሳ ከሚኖርበት ሀገር ውጭ ያለ ወይም ያለች፣ ያልቻለ ወይም እነዚህ ስጋቶች ያሉበት፣ ለመመለስ ፈቃደኛ ያልሆነ፡፡

የስደተኛ ሁኔታን ማግኘት እንይችሉ የሚገለሉ የተወሰኑ ቡድኖች አሉ (**ክፍል 2.8 ይመልከቱ**)፡፡

## 2.5 ለንዑስ ጥበቃ ብቁ የሚሆነው ማነው?

2.5.1 ይህ ከስደተኛ ሁናቴ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ለስደተኛነት ብቁ የማይሆን ሰው ሊያገኘው ይችላል ነገር ግን ይህ የሚሆነው አይፒአ ሰውየው/ሴትየዋ ወደ መጣበት/መጣችበት ሀገር ከተመለሰ/ከተመለሰች ከፍተኛ ጉዳይ ሊያጋጥመው/ሊያጋጥማት ይችላል ብሎ ካመነ ነው፡፡

*ለንዑስ ጥበቃ ብቁ የሆነ ሰው ለሚለው ትክክለኛ ፍቺ ሰውየው*

(i) የአውሮፓ ህብረት አባል ሀገራት ዜግነት የሌለው፣

(ii) ለስደተኛነት ብቁ ያልሆነ፣

(iii) ወደ መጣበት ሀገር/ቀድመው የኖርበት የነበረው ሀገር ቢመለስ ወይም ብትመለስ፣ ከፍተኛ ጉዳት ይደርስብኛል፣ ወይም፣ እነዚህን ስጋቶች መቋቋም ወይም መያዝ አልችልም፣ ብሎ የሚያምን ወይም የምታምን፣ የሀገሩን ጥበቃ የማይፈልግ ወይም የማትፈልግ ከሆነና ይህንንም በተጨባጭ ማሳየት የሚችል እና

(iv) በተወሰኑ ምክንያቶች ከንዑስ ጥበቃ ብቃት ያልተገለለ፡፡ እባክዎን አንቀጽ **2.8.2** ይመልከቱ፡፡

## 2.6 ከፍተኛ ጉዳት ምንድነው?

2.6.1 *ከፍተኛ ጉዳት ማለት፡-*

(i) የሞት ፍርድ ወይም የሞት ቅጣት

(ii) ስቃይ ወይም ኢሰብአዊ አያያዝ ወይም ዝቅተኛ አያያዝ ወይም የመጡበት ሀገር/ቀድመው የኖሩበት የነበረው ሀገር ቅጣት የተጣለበት ወይም የተጣለባት፣ ወይም

(iii) በግለሰብ ህይወት ላይ ከፍተኛና የተናጠል ማስፈራራት ወይም በአለም አቀፍ ወይም በትጥቅ በታገዘ የውስጥ ግጭት ያለልዩነት የማጥቃት ሁኔታዎች፡፡

## 2.7 ወደ መጡበት የመመለስ ክልከላ ምንድነው?

2.7.1 ወደ መጡበት መመለስ ክልከላ ማለት ሚኒስቴሩ ሰውየውን ከግዛቱ አያባርርም ወይም እንዲመለስ አያደርግም፣ በሚኒስቴሩ ሀሳብ፣

(i) ግለሰቡ ሕይወት ወይም ነጻነት ከዘሩ፣ ሀይማኖቱ፣ ዜግነቱ፣ ከተወሰነ የማህበረሰብ ቡድን አባል ወይም የፖለቲካ አመላካከት ችግር ላይ ሲወድቅ፣ ወይም

(ii) በግለሰቡ ከፍተኛ ስጋት ያለበት ከሆነ ይህም እንደ የሞት ፍርድ የተፈረደበት፣ ስቃይ ወይም ሌላ ኢሰብአዊ አያያዝ ወይም ዝቅተኛ አያያዝ ወይም ቅጣት፡፡

ግለሰቡ የስደተኛ ሁናቴ ወይም ንዑስ ጥበቃ ተቀባይነት ቢያገኝም ባያገኝም ሚኒስቴሩ ለስራው ታዛዥ መሆን አለበት፡፡

## 2.8 ከአለም አቀፍ ጥበቃ የሚገለለው ማነው?

2.8.1 ግለሰቡ ከስደተኛነት የሚገለለው፡-

(i) ከአካላት ወይም የተባበሩት መንግስታት (ከተባበሩት መንግስታት ከፍተኛ የስደተኞች ከሚሽነር (ዩኤንኤችሲአር) ውጪ)፣ እንደ ተባበሩት መንግስታት የረፍትና ስራዎች ኤጀንሲ (ዩኤንአርደብሊውኤ) ኤጀንሲዎች ጥበቃ ወይም ድጋፍ ሲደረግለትና ጥበቃው ወይም ድጋፉ ካልተቋረጠ፡፡

(ii) እርሱ ወይም እርሷ የሀገሪቱን ዜግነት ከማግኘት ጋር የተያያዙ መብቶች እና ግዴታዎች ወይም ከዚያ ጋር ተመጣጣኝ የሆኑ መብቶች እና ግዴታዎች እንዳለዉ/እንዳላት የነዋሪነት መብት ባገኘበት/ባገኘችበት ሀገር አግባብነት ባላቸዉ ባለስልጣናት እዉቅና ከተሰጠው/ከተሰጣት፡፡

(iii) ማግለሉን ለመመልከት ከፍተኛ ሆነ ምክንያቶች ካሉበት ወይም ካለባት ይህም፡-

ሀ. ሆነ ብሎ ወንጀል መስራት፣ የጦር ወንጀል፣ በሰብአዊ ፍጡር ላይ ወንጀል መፈጸም፣ በአለም አቀፍ ደረጃ ፍቺው በተቀመጠው መሰረት በእንደነዚ ያሉ ወንጀሎች የተሳተፈ፣

ለ. ወደ ስቴቱ (አየርላንድ) ከመምጣቱ ቀደም ብሎ ከስቴቱ (አየርላንድ) ውጪ ፖለቲካዊ-ያልሆነ ለባድ ወንጀል የፈጸመ፣ ወይም

ሐ. ከተባበሩት መንግስታት አላማዎችና መርሆች በተጻራሪነት ጥፋተኛ የሆነ፡፡

እባክዎን ያስታውሱ፣ ግለሰቡ በወንጀል ወይም በ (iii) ሕግ እንደተጠቀሰው ከፍተኛ ወንጀል ያነሳሳ ወይም የተሳተፈ ከሆነ በሂደቱ ላይጠቃለል ይችላል፡፡

2.8.2 ግለሰቡ በንዑስ ጥበቃ ስር እንዳይጠቃለል ወይም እንዳትጠቃለል ሊየደርግ የሚችለው ከፍተኛ ምክንያት፡-

(i) ሆነ ብሎ ወንጀል መስራት፣ የጦር ወንጀል፣ በሰብአዊ ፍጡር ላይ ወንጀል መፈጸም፣ በአለም አቀፍ ደረጃ ፍቺው በተቀመጠው መሰረት በእንደነዚ ያሉ ወንጀሎች የተሳተፈ፣

(ii) ከፍተኛ ወንጀል የፈጸመ፣

(iii) ከተባበሩት መንግስታት አላማዎችና መርሆች በተጻራሪነት ጥፋተኛ የሆነ፣ ወይም

(iv) ለማህበረሰቡ ወይም ለስቴቱ (አየርላንድ) ደህንነት አደገኛ የሆነ፡፡

እባክዎን ያስታውሱ፣ ግለሰቡ በወንጀል ወይም በ (i) – (iv) ሕግ እንደተጠቀሰው ከፍተኛ ወንጀል ያነሳሳ ወይም የተሳተፈ ከሆነ በሂደቱ ላይጠቃለል ይችላል፡፡

2.8.3 ግለሰቡ ከንኡስ ጥበቃ ሊገለል ወይም ልትገለል የምትችልበት፣ ወደ ስቴቱ (አየርላንድ) ከመምጣቱ ወይም ከመምጣቷ በፊት፣ **በአንቀጽ 2.8.2** ያልተገለጸ ወንጀል ከፈጸመ፣ በስቴቱ (አየርላንድ) ተፈጽሞ ከሆነ፣ በእስር የሚያስቀጣ ሆኖ ከመጣበት ወይም ከመጣችበት የመጡበት ሀገር/ቀድመው የኖሩበት የነበረው ሀገር ይህንን የወንጀል ቅጣት ለማስቀረት የሆነ እንደሆነ፡፡

## 2.9 ኢዩአርኦዲኤሲ ምንድነው?

ኢዩአርኦዲኤሲ በስቴቶቹ ስምምነት መሀል ውጤታማ የኢዩ ደብሊን ደንበቦች ማመልከቻ እንዲኖር አሻራን የሚለዋወጡበትና የሚያወዳድሩበት ነው፡፡ ስለ ኢዩ ደብሊን ደንቦች መረጃን ለማግኘት **ክፍል 10** ይመልከቱ፡፡

## 2.10 የጋራ የጉዞ ቦታ ክልል ምንድነው?

2.10.1 የጋራ የጉዞ ቦታ (ሲቲኤ) አየርላንድን፣ ዩናይትድ ኪንግደም፣ ቻናል አየስላንድስ እና ዘ አይስ ኦፍ ማንን በአንድ ላይ ይይዛል፡፡

## ክፍል 3
## የአለም አቀፍ ጥበቃ ሂደት

### 3.1 ለአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዬን ካስገባሁ በኋላ ምን መጠበቅ እችላለሁ?

3.1.1 ለአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዎን ካስገቡ በኋላ እነዛን መጠበቅ ይችላሉ፡-

(i) የሚሰተናገዱት ጾታ፣ አካል ጉዳት፣ ዜግነት፣ ጎሳ፣ ዘር፣ ጾታ፣ የፆታ ግብዛቤ፣ ሀይማኖት ወይም እምነት ምንም ሆነ ምን በአክብሮትና በፍትሀዊነት ይስተናገዳሉ፡፡

(ii) አይፒኦ ይህ ሂደት ለርሶ ያልተለመደና አርሶም በአሰቃቂ ሁኔታ ያለፉና ስለራሶት ያለውን ስስ መረጃ ለማጋራት ሊከብዶት እንደሚችል ይረዳል፡፡

(iii) ማመልከቻዎትን በመቀበል የግል ጉዳዮት ከግምት እንዲገባ፣ አይፒኦ ለማመልከታዎት የሚጠቅሙ ስስ የሆነ መረጃዎትን ለምሳሌ፣ ስለ መደፈር፣ ስቃይ፣ ማንኛውም አይት የህመም ህክምና፣ ወይም ጾታዎት በማጋራቶት ደህንነት እንዲሰማዎት ይፈልግል፡፡ ከማመልከቻዎት ጋር ግንኙነት ያላቸው ሁሉም ዝርዝር መረጃዎች በሕጉ መሰረት በምስጢር የሚያዙና ለሀገሮት ባለስልታናት ወይም በአየርላንድ ላለው የሀገሮት ተወካይ የማይጋራ ነው፡፡

(iv) የሚቻል ከሆነና፣ ለእርሶ ጉዳይ ወንድ ወይም ሴት ማናገር የሚቀሎት ከሆነ፣ አይፒኦ ይህንን ጥያቄ ይቀበላል፡፡

(v) አይፒኦ ለማናገር እንግሊዘኛ ደስ ያሰኞት እንደሆን ወይም አስተርጓሚ የሚያስፈልጎት እንደሆን ይጠየቃሉ፡፡ አስፈላጊና የሚቻል ከሆነ፣ ተገቢው ንግግር መደረጉን ለማረጋገጥ አስተርጓሚ እንዲያመጡ ይፈቀድሎታል፡፡

### 3.2 የማመልከቱ ሂደት የመጀመሪያው እርምጃ ምንድነው?

3.2.1 ለአለም አቀፍ ጥበቃ ከማመልከተቶት በፊት ማመልከቻዎት በአይፒኦ ተቀባይነት ሊኖረው እንደሚችል ወይም እንደማይችል ለማወቅ የቅድመ ቃለመጠይቅ ማጠናቀቅ እንደሚኖርቦት በጥቅ እናሳስባለን፡፡

### 3.3 ማመልከቻው ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችለው እንዴት ነው?

3.3.1 ለአለም አቀፍ ጥበቃ ከማመልከቶት በፊት፣ የቅድመ ቃለመጠይቁ አካል ነው፣ ማመልከቻዎት ተቀባይነት ሊኖረው የመቻሉ ነገር ላይ የአለም አቀፍ መኮንኑን ማርካት አለበት፡፡

3.3.2 ማመልከቻዎት ተቀባይነት የማይኖረው (እንዲሁም ለጥበቃው ማመልከት የማይችሉት)፡-

(i) ሌላ የኢዩ አባል ሀገር የርሶን የስደተኛነት ሁኔታ ወይም ንዑስ ጥበቃ ተቀብሎ ከሆነ እና/ወይም

(ii) ከኢዩ አባል ሀገራት ሌላ

ሀ. እንደ ስደተኛ የሚቆጥሮትና አሁንም በዛ ጥበቃ ስር ያሉ ከሆነ፣ ወይም

ለ. በዛ ሀገር አጥጋቢ ጥበቃ የሚደረግሎት እንደሆነ፣ ይህም በመርህ ደረጃ በግዳጅ-ያለማስመለስና በሀገሮት እንደገና ተቀባይነት ማግኘትን ይጨምራል፡፡

3.3.3 አለም አቀፍ ጥበቃ መኮንኑ ከቅድመ ቃለ መጠይቁ በኋላ ማመልከቻዎት ተቀባይነት እንዲኖረው ምክረ ሀሳቡን ይሰጣል፡፡

3.3.4 ለአለም አቀፍ ጥበቃ ያስገቡት ማመልከቻ ተቀባይነት ካላገኛ ከአለም አቀፍ ጥበቃ መኮንኑ ግብረ መልስ ማግኘት ይኖርቦታል፣ ምክንያቶቹን የያዘ ሪፖርት በጽሁፍም ይደርሶታል፡፡

3.3.5 በተገቢው የህግ ወቅት ለአይፒኤቲ ግብረ መልስ ላይ ይግባኝ መጠየቅ ይችላሉ፡፡ ስለ ይግባኝ የበለጠ መረጃ **በክፍል 5** ይገኛል፡፡ **የኤፒኤቲ ውሳኔ በቃል ሳይሰማ የሚሰጥ ይሆናል፡፡**

3.3.6 የአለም አቀፍ ጥበቃ መኮንኑ ግብረ መልስ መሰረት ተቀባይነት ካላገኙ፣ እንዲሁም ግብረ መልሱ በአይፒኤቲ ከተረጋገጠ፣ ሚኒስቴሩ ማመልከቻዎትን ላለመቀበል ይወስናል፡፡

3.3.7 ማመልከቻዎት በአይፒኦ ወይም በአይፒኤቲ ተቀባይ ሆኖ ከተገኘ፣ በሚኒስቴሩ በአይፒኦ በኩል ለምርመራና ውሳኔ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

## 3.4 ለአለም አቀፍ ጥበቃ ቀድሜ ባመለከትኩት ላይ ውሳኔ ደርሶኛል፣ ሌላ ማመልከቻ ማስገባት እችላለሁ (ተከታይ ማመልከቻ)?

3.4.1 ያለ ሚኒስቴሩ ፈቃድ በስተቀር ግለሰቡ ለአለም አቀፍ ጥበቃ ሁለተኛ ወይም አራተኛ ማመልከቻ ማስገባት አይችልም (*ተከታይ ማመልከቻ*)፡፡

3.4.2 በሚኒስቴሩ ዘንድ እሺታን እንዲያገኝ ለአለም አቀፍ ጥበቃ የሚገባው የተከታይ ማመልከቻ ለሚኒስቴሩ መጻፍ ይኖርበታል እንዲሁም በአለም አቀፍ ጥበቃ መኮንኑ ከግምት መግባት አለበት፡፡

3.4.3 የተከታይ ማመልከቻ ፈቃድ ለማግኘት፣ የሚከተሉት ሁኔታዎች ከግምት መግባት አለባቸው፡-

(i) በቀደመው የአለም አቀፍ ማመልከቻ ውሳኔ ላይ አዲስ መረጃ ወይም ግኝት ሲነሳ ወይም ለአለም አቀፍ ጥበቃ ሊያበቃ የሚችል ጉልህ የሆነ ነገር ሲገኝ፣

እና

ምንም ጥፋት ካልሰሩ፣ ለማመልከቻዎት ሲባል እነዚህን ማስረጃዎች ወይም ለቀደመው ማመልከቻዎት የሚውሉ ግኝቶች ማቅረብ ካልተቻለ

*ወይም*

(ii) የበፊቱ ማመልከቻ ከቀረ ወይም እንደቀረ ከተቆጠረ፣ እርሶ፣ በቀረበት ወይም እንደቀረ በተቆጠረበት ግዜ፣ የእርሶ ጥፋት ካልሆነ፣ የቀደመውን ማመልከቻዎትን ማስቀጠል ካልቻሉ፡፡

3.4.4 የአለም አቀፍ ጥበቃ መኮንኑ ሚኒስቴሩ ለተከታይ ማመልከቻ እሺታን ሲሰጥ ግብረ መልሱን ይሰጣል፣ በዚህም ሚኒስቴሩ ይፈቅድና እርሶም ማመልከቻውን ማስገባት ይችላሉ፡፡

የአለም አቀፍ ጥበቃ መኮንኑ በግብረ መልሱ በተከታይ ማመልከቻዎት ላይ ለሚኒስቴሩ እሺታውን *እንዳይሰጥ* ወይም *ስንዳትሰጥ* ካደረገ፣ የዚህ ምክንያት በጽሁፍ ይደርሶታል፡፡

3.4.5 በተገቢው የህግ ወቅት ለአይፒኤቲ የይግባኝ ደብዳቤዎትን ማስገባት ይችላሉ፡፡ ስለ ይግባኝ የበለጠ መረጃ **በክፍል 5** ይገኛል፡፡ **የኤፒኤቲ ውሳኔ በቃል ሳይሰማ የሚሰጥ ይሆናል፡፡** ይግባን ካላሉ፣ ሚኒስቴሩ ተከታይ ማመልከቻዎትን አይቀበልም፡፡

3.4.6 ይግባኞት የተሳካ ከሆነ፣ ሚኒስቴሩ ተከታይ ማመልከቻ እንዲያስገቡ ይፈቅድሎታል፡፡ ለአይፒኤቲ ያስገቡት ማመልከቻ የተሳካ ካልሆነ፣ ሚኒስቴሩ ተከታይ ማመልከቻዎትን አይቀበልም፡፡

## 3.5 *የመጀመሪያው ቃለ መጠይቅ ምንድነው?*

3.5.1 ቅድመ ቃለመጠይቁን ሲያጠናቅቁ፣ ከሌሎች ነገሮች ጋር፣ ጥያቄዎች ይቀርብሎታል፣ የተወሰኑት አጫጭር ጥያቄዎች

(i) ለአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከት ይፈልጉ እንደሆነ፣ ከፈለጉ፣ የትኛው ማመልከቻን መሰረት ማድረግ እንዳለበት አጠቃላይ መነሻ፣
(ii) መታወቂያዎት፣
(iii) ዜግነቶት፣
(iv) ስለ መጡበት ሀገር/ቀድመው ይኖሩበት የነበረው ሀገር፣
(v) ወደ ስቴቱ (አየርላንድ) የመጡበት መንገድ፣ የተጠቀሙት መጓጓዣና ወደ አየርላንድ እንዲመጡ የረዳዎትን ግለሰብ ዝርዝር፣
(vi) ወደ አየርላንድ የመጡበት ምክንያት፣
(vii) ወደ ስቴቱ (አየርላንድ) የገቡበት ወይም የተገኙበት ህጋዊ መሰረት፡፡

3.5.2 ለአለም አቀፍ ጥበቃ ሂደት ተቀባይነቶትን ለመወሰን አንዳንድ ጥያቄዎችን ይጠየቃሉ (**ክፍል 3.3 እና 3.4 ይመልከቱ**)፡፡

3.5.3 ይህ ቅድመ ቃለመጠይቅ፣ አስፈላጊ ከሆነ ወይም ከተቻለ፣ በአስተርጓሚ አማካኝነት ይደረጋል፡፡

3.5.4 የዚህ ቅድመ ቃለመጠይቅ ቅጂ መጠይቁን ባካሄደው መኮንን ዘንድ የሚቀመጥ ይሆናል፡፡ ይህም ለርሶ መልሶ የሚደመጥና አስፈላጊ ከሆነም እርማት እንዲያደርጉም እድሉን ይሰጦታል፡፡ የሰጡት መረጃ ትክክለኛና አስፈላጊው ማስተካከያና ለውጦች የተደረጉበት መሆኑን የሚያረጋግጥ መግለጫ ላይ ፊርማዎትን እንዲያኖሩ ይጠየቃሉ፡፡ የሰጡት አስፈላጊ መረጃ በትክክል መካተቱን ለማረጋገጥ መግለጫውንም በጥንቃቄ በማንበቡ በጣም ጠቃሚ ነገር ነው፡፡ በቃለመጠይቁ ወቅት የተዛባ ወይም አለመግባባት እንዳይኖር የማድረጉ ሀላፊነት የርሶ ነው፡፡ ከዛም የተስማሙበት የዚህ ቃለመጠይቅ ቅጂ ይሰጦታል፡፡

3.5.5 ከዚህ የቅድመ ቃለመጠይቅ ተከትሎ፣ ማመልከቻዎት ተቀባይ ከሆነ፣ የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ለአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከት ይችላሉ፡፡

## 3.6 የጣት አሻራና ሌሎች የባዮሜትሪክ መረጃዎችን መውሰድ አለብኝ?

3.6.1 አይፒኦ የባዮሜትሪክ መረጃዎትን ይወስዳል፡፡ ይህም የጣት አሻራዎትንና ፎቶግራፎትን ያካትታል፡፡ ይህ ማንነቶትን ለመመስረትና በስምምነት ስቴት የኢዩ ደብሊን ደንቦች (**ክፍል 10 ይመልከቱ**) ቀደም ብሎ ለአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከትና አለማመልከቶትን ለማረጋገጥ ነው፡፡ መረጃው ከመረጃ ቋታችን (ኢዩአርኦዲኤሲ እና ቪዛ) ጋር ተያይቶ አየርላንድ ማመልከቻዎትን የምታይ ብቸኛ ሀገር መሆኗን ለማረጋገጥ ይረዳል፡፡

እድሜአቸው ከ 14 አመት በታች ለሆኑ የጣት አሻራቸው የሚወሰደው ወላጅ ወይም ሀላፊነት ያለበት አዋቂ ሰው ባለበት ወይም፣ ከተቻለ፣ በቲዩኤስኤልኤ - የልጆችና ቤተሰብ ኤጀንሲ በተሰየመው ሰው ማመልከቻ ማስገባትና በሂደቱ ግዜ ማመልከቻውን ያቀርባል፡፡

## 3.7 ከአለም አቀፍ ጥበቃ ሂደት የጽሁፍ መረጃ ይደርሰኛል?

3.7.1 ከዚህ መጸሀፍ ጋር ለአይፒኦ ተሞልቶ የሚመለስ የአለም አቀፍ ጥበቃ መጠይቅ ማመልከቻ ይሰጦታል፡፡ በአይፒኦ በተገለጸው ቀንና ሰአት መሰረት መጠይቁን ይመልሱ፡፡

<u>**በተጠቀሰው ቀን መጠይቁን ሳይመልሱ ከቀሩ፣ በማመልከቻዎት ምርመራ ላይ ተባባሪ ሳይሆኑ ቀርተበዋል ማለት ነው፡፡ በዚህ ረገድ፣ እባክዎን ክፍል 4.4 እና ክፍል 8.2 ይመልከቱ፡፡**</u>

3.7.2 መጠይቁን ከማጠናቀቆት በፊት የህግ ምክር እንዲያገኙ እንመክራለን፡፡

## 3.8 ለአለም አቀፍ ጥበቃ ሳመለክት ምን ይዤ መምጣት አለብኝ?

3.8.1 ለማመልከቻዎት የሚረዳ በእጆት ያሉ ማንኛውንም አይነት ሰነዶች ይዘው ወደ አይፖኦ ያምጡ፡፡ ዝነዚህ የሚያጠቃልሉት፡-

- **ፓስፖርት (ቶች)** - ይህ የሚያካትተው የእርሶን ፖስፖርት፣ ያባለቤቶትን እና/ወይም አብሮት በጥገኝነት በአየርላንድ አብሮት ያለን (የሚኖር ከሆነ) ሰው ፓስፖርት፡፡ ይህ አይፒኦ እድሜዎትን፣ ማንነቶትንና ዜግነቶትን እዲመሰርት ይረዳዋል፡፡ ወደ አየርላንድ ባደረጉት ጠቅላላ ወይም በተወሰነው ጉዞ ሀሰተኛ ፓስፖርት ተጠቅመው ከሆነ እሱን ይዘው ይምጡ፡፡

- **ማንኛውንም አይነት የጉዞ ሰነድዶች** - ይህ ጉዞ ካደረጉበት ፓስፖርትና የዜግነት ማንነት ጋር ባይመሳሰልም እንኳ የጉዞ ትኬትን፣ የመሳፈሪያ ትኬትን ያጠቃልላል፡፡

- **ሌሎች ሰነዶች** - ይህ የሚያካትተው የመታወቂያ ካርድን፣ የልደት/ጋብቻ/የትምህርት ሰርተፍኬቶችን፣ የአባልነት መታወቂያዎችና ከሚጠቅሱት ነገር ጋር ግንኙነት ያለው ማንኛውንም ነገር ነው፡፡

3.8.2 ማመልከቻዎትን **በተቻለ ፍጥነት** ማመልከቻዎትን ሊደግፍ የሚችል **ሊገኝ የሚችል ዶክመንት** ለአይፒኦ ያቅርቡ፡፡ ወደ አይፒኦ ይዘዋቸው ይምጡ ወይም ለአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዎትን ሲያስገቡ ይህንን ማድረግ ሳይችሉ ከቀሩ፣ ለአለም አቀፍ ጥበቃ ከመታየቱ በፊት በቻሉት ፍጥነት ያቅርቡአቸው፡፡ እነዚህን መስፈርቶች ሳያሟሉ የቀሩ እንደሆነ፣ ለአለም አቀፍ ጥበቃ እንዲታይ በቀረበው ግዜ ውስጥ ለአይፒኦ ማንኛውንም አይነት ተጨማሪ ሰነድ ያስገቡ፡፡

3.8.3 ከሁኔታዎች ጋር በተያያዘ፣ ሰነዶችን ሳያቀርቡ መቅረት የሚያመለክተው ለአለም አቀፍ ጥበቃ ሂደት **ለመተባበር ድርሻዎትን እንዳልተወጡ** ነው፡፡ እባክዎን **ክፍል 4.4 እና ክፍል 8.2** ይመልከቱ፡፡

## 3.9 የግዜአዊ መኖሪያ ሰርተፍኬት (ቲአርሲ) ምንድነው፣ መቼስ ነው የምቀበለው?

3.9.1 ለአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዎትን ሲያስገቡና ማመልከቻውም ተቀባይነት ሲያገኝ፣ እንደ ቅድመ ምዝገባ ሂደት አካል የግዜአዊ መኖሪያ ሰርተፍኬት(ቲአርሲ) ያገኛሉ፡፡ ቲአርሲ ለአየርላንድ የጥበቃ ማመልከቻ ለማስገባትዎት ማስረጃ ነው፡፡

3.9.2 ቲአርሲ የመታወቂያ ካርድ **አይደለም** እንዲሁም የማንነቶት መግለጫ ማረጋገጫ አይደለም ነገር ግን ለአይፒኦ ያቀረቡት የግል ዝርዝር የያዘ፣ ይህም ስሞትን፣ የትውልድ ቀንንና ዜግነትን እንዲሁም ፎቶግራፎትን ያጠቃልላል፡፡

3.9.3 ቲአርሲ፣ የሚታደስ፣ የሚኒስቴሩ ንብረት የሆነና በሚኒስቴሩ ሲጠየቁ መመለስ ይኖርቦታል፡፡ ቲአርሲ ዋጋ የሚጣያው በስቴቱ (አየርላንድ) መግባትና የመኖር ፈቃድ ጥበቃ ማመልከቻው ውድቅ ሲደረግ ነው፡፡

3.9.4 እባክዎን ቲአርሲ የሚያሳየው በስቴቱ (አየርላንድ) ፈቃድ ለማግኘት ለአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻውን የሚያገለግል በመሆኑ በግዜው መሰረት የተሻሻለ መሆኑን ያረጋግጡ፡፡

## 3.10 የአካል ጉዳት ቢኖርብኝ ወይም ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልገኝ ከሆነ ምን ይሆናል?

3.10.1 እባክዎን በቻሉት ፍጥነት በቃለመጠይቁ ወቅት ለአይፒኦ የልዩ ፍላጎቶቹን ወይም ቅድመ ሁኔታዎቹን ያሳውቁ፡፡ እንዲሁም ለአይፒኦ ማመልከቻዎትን ባስገቡበት ቀን ያለውን የልዩ ፍላጎቶች ያሳውቁ፡፡ ከተቻለ፣ ባሳወቁት መሰረት አይፒኦ በሚያስፈልጎት መሰረት የሚርፉበትን እንዲያገኙ ይሞክራል፡፡

## 3.11 በጥበቃ ስር ወይም በእስር እያለሁ ለአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከት እችላለሁ?

3.11.1 በስቴት (አየርላንድ) በጥበቃ ስር ወይም በእስር ቢሆኑም አንኳ ለአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከት ይችላሉ፡፡ የጥበቃ ማመልከቻዎትን በታሰሩበት ገዢው ኢኒስቲቲውት በኩል ብቻ ማስገባት ይችላሉ፡፡ ለጥበቃው ማመልከቻ ማስገባት እንደሚፈልጉ ለገዢው ቢሮ ወዲያውኑ ያሳውቁ፡፡ የገዢው ቢሮ ከአይፒኦ ጋር በመሆን ማመልከቻዎት እንዲሄድ አስፈላጊውን ዝግጅት ያደርጋል፡ ፡

3.11.2 አይፒኦ በእስር ያለውን ግለሰብ ማመልከቻ ምርመራና ውሳኔውን ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

## 3.12 ለአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካች የሚታሰርበት ሁኔታ ምንድነው?

3.12.1 የፍልሰት መኮንኑ ወይም የግራዳ ሲቻና አባል አሳማኝ ምክንያግ ካገኙ፣ አመልካቹን ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ በቁጥጥር ስር ያውሉታል፣ አሳማኝ አጠራጣሪ ምክንያቶቹ፡-

(i) በስቴቱ (አየርላንድ) ውስጥ የህዝብ ደህንነት ወይም የህዝብ ደነቦችን ስጋት ላይ ሲጥል፣

(ii) ከስቴቱ (አየርላንድ) ውጭ ከባድ ወንጀል የፈጸመ እንደሆነ፣

(iii) በማንነቱ ላይ በቂ የሆነ ምክንያት ያላቀረበ ወይም ያላቀረበች፣

(iv) ስቴቱን (አየርላንድን) የሚለቅና ያለ ሕጋዊ ፈቃድ ሌላ ስቴት የገባ፣

(v) እነዚህን ከግምት ባለማስገባት ያደረገ ወይም ሊያደርግ የነበረ -

- ግለሰብን በስቴቱ (አየርላንድ) ለአለም አቀፍ ጥበቃ የሚያበቃ ሲስተም፣ ወይም
- ከጋራ ጉዞ ቦታ ጋር የሚገናኝ ማንኛውም አይነት ዝግጅት (**ክፍል 2.10** ይመልከቱ)፣ ወይም

(vi) ያለ በቂ ምክንያት -

- መታወቂያውን/መታወቂያዋን ወይም የጉዞ ሰነዱን/ሰነዷን ያጠፉ/ያጠፉች፣ ወይም
- የሀሰተኛ ሰነድ፣ የተለወጠ ወይም የተቀየረ የመታወቂያ ሰነድ መያዝ፡፡

3.12.2 እርስዎ ከታሰሩ ወይም ከላይ ከተጠቀሱት ማንኛውም ቢከሰት ወደ ታዘዘ ማቆያ ቦታ ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡ የታሰረ ሰው በተቻለ ፍጥነት ለሁለት ቀን እስራት ወይም በእውነታዎች መሰረት ግለሰቡ እንዲለቀቅ ውሳኔ ሊያስተላልፍ የሚችለው የዲስትሪክት ፍ/ቤት ፊት መቅረብ ይኖርብዎታል፡፡ የእስራት ጊዜ ከጊዜ ወደ ጊዜ ለአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ውሳኔ ላይ ተሞርክዞ እስከ 21 ቀን ሊሻሻል ይችላል፡፡ በዚህ አንቀጽ መሰረት የታሰረ ሰው የህግ ተወካዩን ማነጋገርና ከህግ አማካሪው ጋር ለሚያደርገው ምክክር ፍ/ቤት ሲቀርብ ያስተርጓሚው እገዛ የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡

## 3.13 በእኔ ላይ ጥገኛ ሆነው የሚኖሩ ከ18 ዓመት በታች ካሉስ?

3.13.1 የስቴት (አየርላንድ) ዜጋ ያልሆነ/ያልሆነች ከ18 ዓመት በታች ዕድሜ የሆነ/የሆነች በእርስዎ ማመልከቻ ውስጥ መካተት አለበት/አለባት፡፡ ይህ እሳቤ እርስዎ ማመልከቻ በሚያስገቡበት ጊዜ ህጻኑ በአየርላንድ ወስጥ የሚኖር ወይም የማይኖር ከገሆነ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

3.13.2 ስለሆነም፣ ለአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ሲያስገቡ፣ የአየርላንድ ዜጋ ላልሆነ ጥገኛ ልጆትም ማመልከቻ እንዳስገቡ ይቆጠራል፣ እንዲሁም

(ሀ) በማመልከቻው የሚቀርብበት ጊዜ በስቴቱ (አየርላንድ) ውስት ያለ ሆኖ ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ እንደሆነ፣

(ለ) እርስዎ አመልካች ሆነው እያሉ በስቴቱ (አየርላንድ) ውስጥ የተወለደ እንደሆኑ፣

(ሐ) እርስዎ አመልካች እያሉ በስቴቱ (አየርላንድ) ዕድሜው 18 ዓመት ሆኖ ወደ አየርላንድ የገባ እንደሆነ፣ ከእርስዎ ጋር የሚኖር ህጻንም እንዲሁ ማመልከት ይኖርብዎታል፡፡

3.12.3 እርስዎ አብርዎት ለሚኖር ልጅዎ ለአለም አቀፍ ጥበቃ እያመለከቱ ከሆነ ማመልከቻ ሲያቀርቡ ወደ አይፒኦ እንዲሁም ይዘው መምጣት ካልብዎት

3.13.4 **ጠቃሚ ማስታወሻ፡- ህጻኑ እርስዎ ለአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ካቀረቡ በኋላ የተወለደ ከሆነ ወይም ማናቸውም ከእርስዎ ጋር የሚኖሩ ሰዎች እርስዎ ማመልከቻ ካቀረቡ በኋላ ወደ ስቴት (አየርላንድ) የገቡ ከሆነ ህጻኑ /ህጻናቱን ወዲያውኑ ይዞ ወደ አይፒኦ መምጣት ይኖርብዎታል፡፡**

## 3.14 የህግ ምክር ከየት አገኛለሁ?

3.14.1 የአለም አቀፍ ጥበቃ ለመጠየቅ የሚያቀርቡትን ማመልከቻ በተመለከተ የህግ አማካሪዎን የማነጋገር መብት አለዎት፡፡ የህግ ድጋፍ ቦርድ (ኤልኤቢ) የሚከተሉትን አገልግሎቶች ማግኘት ይችላሉ፡-

(i) የእርስዎ ማመልከቻ በመደገፍ የሚሰጠውን የህግ እገዛና ምክር፡፡

(ii) እርስዎ ሚኒስቴሩ በስቴት (አየርላንድ) ወስጥ እንዲቆዩ ፍቃድ እንዲሰጥዎ ለመጠየቅ የሚያነሷቸውን ማናቸውም ምክንያቶች ጨምሮ የአለም አቀፍ ጥበቃ መጠይቅዎን እንዲሞሉ ለማስቻል የሚሰጠውን ምክር

(iii) የአለም አቀፍ ጥበቃ ቃለመጠይቅዎ እና ለሚኒስቴሩ በጹሁፍ የሚቀርቡትን መረጃ ለማዘጋጀት የሚያደርግልዎትን እገዛ፡፡

(iv) በማመልቻው ላይ አሉታዊ የውሳኔ ሃሳብ ከቀረበ ለአይፒኤፒ በሚያቀርቧቸው ማናቸውም የሚያቀርቧቸውን ይግባኖች በተመለከተ የህግ ተወካይ በመቅረብ የሚሰጥዎትን ድጋፍ፡፡

3.14.2 የኤልኤቢ ዝርዝር አድራሻ በዚህ ሰነድ ወስጥ **በቅጥያ** ላይ ተካቷል፡፡

3.14.3 የኤልኤቢ አገልግሎቶች መጠቀም የማይፈልጉ ከሆነ በራስዎ ወጪ የግል የህግ አማካሪ እንደአማራጭ መጠቀም ይችላሉ፡፡ በግልዎ የህግ አማካሪ ማማከር ከፈለጉ በስቴቱ (አየርላንድ) ውስጥ በህግ ጥብቅናና እና ምክር የተመዘገበ/የተመዘገበች መሆኑን ያረጋግጡ፡፡

### 3.15 ለአለም አቀፍ ጥበቃ ያስገባሁትን ማመልከቻ ማቆም እችላለሁ?

3.15.1 የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዎትን የአለም አቀፍ ጥበቃ መኮንኑ ሪፖርቱን ከማዘጋጀቱ በፊት መተው ይችላሉ፡፡ ማመልከቻውን ማቆሞትን የሚገልጽ ማስታወቂያ ለአይፒኦ በመላክ ማስቆም ይችላሉሉ፡፡ ማስታወቂው የመጨረሻ አድራሻዎትን፣ የማጣቀሻ ቁጥርንና ፊርማዎትን መያዝ ይኖርበታል፡፡ በእርሶ ስር ጥገኛ የሆኑ ልጆች በማመልከቻው ከተጠቃለሉ፣ በማስቆሚያ ማመልከቻው ላይ ዝርዝሩ መጠቃለል አለበት፡፡

3.15.2 የእርስዎ ማመልከቻ ከወጣ ለአይፒኤፒ የሚያቀርቡት ይግባኝ የማይኖር ሲሆን ሚኒስቴሩም የስደተኛ ሙብት ወይም የንዑስ ጥበቃ ማረጋገጫ እንዳይሰጥዎ ይከለክላል፡፡ ነገር ግን እባክዎን ሚኒስቴሩ በሌሎች ምክንያቶች እንዲቆዩ ፈቃድ ሊሰጥዎ እንደሚገባ ወይም እንደማይገባ ግምት ውስጥ የማያስገባ ነው፡፡ በስቴት (አየርላንድ) ውስጥ የሚቆዩበት ሌላ ምክንያት ከሌለ በስተቀር ወደ ሀገርዎ በግዴታ እንዲመለሱ ትዕዛዝ ሊሰጥዎ ይችላል፡፡

3.15.3 የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዎን ከማውጣቱ በፊት የውሳኔዎ የሚያስከትለውን ውጤት ገንዘብዎን ለማረጋገጥ የህግ ምክር ማግኘት ይኖርብዎታል፡፡

## ክፍል 4
## ቃለ መጠይቅ እና ምርመራ

### 4.1 በአለም አቀፍ ጥበቃ ቃለመጠይቁ ላይ ምን ልጠብቅ እችላለሁ?

4.1.1 ስለአለም አቀፍ ጥበቃ ቃለመጠይቅዎ ቀን ፣ ሰዓትና ቦታ መረጃ **በአይፒኦ አማካይነት በጽሁፍ** ይሰጦታል፡፡ ቃለመጠይቁ ለግልዎት ብቻ ይደረጋል፡፡ ወንድ ወይም ሴት ቃለመጠይቅ አድራጊ መኮንን እና /ወይም አስተርጓሚ ከጠየቁ አይፒኦ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሚቻል ሲሆን ይህንኑ ያመቻቻል፡፡

4.1.2 ቃለመጠይቁ ከአይፒኦ ጋር ግምባር ለግምባር ለመነጋገር እና የመጡበት ሀገር/ቀድመው ይኖሩበት የነበረውን ሀገር ለቀው የወጡበትን ምክንያት እና ወደዚያ ለመመለስ የፈሩበትን ምክንያት እንዲገልጹ እድል ይሰጥዎታል፡፡ እኛ በተቻለን መጠን ማራኪና እርግጠኛ የምንሆንበትን ሁኔታ በሚፈጥርበት ቃለመጠይቅዎ ላይ መገኘት በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ምን እንደደረሰቦት ሙሉ መረጃ እና ወደ መጡበት ሀገር/ቀድመው ይኖሩበት የነበረው ሀገር ለመመለስ ማንን ወይም ምንን እንደፈሩ ሙሉ መረጃ በእውነተኛ መንገድ ማስረዳት በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

4.1.3 እኛ ቃለመጠይቅ የምናደርግሎት በመረዳትና መግባባት በሚችሉት ቋንቋ ይሆናል የሚደረግበት ቃለመጠይቅ በአይፒኦ መኮንን አማካይነት የሚመዘገብና ማንኛውም ማስተካከያ ማድረግ እንዲችሉ ወይም ተጨማሪ መረጃ እንዲያካትቱ በየዙሩ ይነበብሎታል፡፡ ከኢንተርቪው በተመዘገበው ሰነድ እያንዳንዱ ገጽ ላይ የሰጡት መረጃ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ይፈርማሉ፡፡

4.1.4 በቃለመጠይቁ ጊዜ (ወይም ከተቻለ ከዚያ ቀደም ብሎ) ማስረጃውን የሚደግፍ ማስረጃ ወይም ማንኛውም መረጃ ቢያቀርቡ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ከቃለመጠይቁ በኋላ ተጨማሪ ማስረጃ ማቅረብ ከፈለጉ በአይፒኦ በተነገርዎት ጊዜ ገደብ ውስጥ ማቅረብ ይኖርቦታል፡፡

4.1.5 ማንኛውም በጾታ ላይ የተመሰረተ እና በማመልከቻው ውስጥ ወይም በምርመራው ሂደት የጠቀሱት ማንኛውም ተጋላጭነት ካለ እንቀበላለን፡፡

4.1.6 **በጥበቃ ቃለመጠይቅዎ ፈቃድ ጋር በተያያዘ በቀጥታ ጥያቄዎችን አይጠየቁም፡፡ ቃለመጠይቁ የጥበቃ ማመልከቻዎ ላይ የሚያተኩር ይሆናል፡፡** ነገር ግን እንዲህአይነት ነገሮች (ለምሳሌ የቤትሰብዎ ሁኔታ) ከተነሳ በአይፒኦ አማካይነት በጸሁፍ የሚቀዳ ይሆናል፡፡ አይፒኦ የአለም አቀፍ ጥበቃ እንዳይሰጥዎ ሀሳብ ካቀረበ በሌሎች ምክንያቶች በጥበቃ ስር እንዲቆዩ ፈቃድ እንደሚሰጥዎ ወይም እንደማይሰጥዎ ለመወሰን ትኩረት የሚሰጥዎ እና በጥበቃ ማመልከቻ ሂደቱ ያቀረባቸው አግባብነት ያላቸው ማንኛውም መረጃዎች በዚያ ጊዜ ግምት ውስጥ የሚገቡ ይሆናል፡፡

## 4.2 የሚረዳኝን ማንኛውንም ሰው ይዤ ወደ አለም አቀፍ ጥበቃ ቃለመጠይቁ መምጣት እችላለሁ?

4.2.1 ቃለመጠይቅ የሚደረግልዎት ለብቻዎት ነው፡፡ የህግ ተወካይዎ በቃለመጠይቁ ላይ መገኘት ይችላል፡፡ ከህግ እርዳታ ቦርድ የህግ ምክር እያገኙ ከሆነ በቃለመጠይቁ ላይ መገኘት እንደሚችና እንደማይችል የህግ ተወካይዎን መጠየቅ አለብዎት፡፡ በአጠቃላይ ዕድሜዎ ከ18 አመት በታች ከሆነ እና የእርስዎ አሳዳጊ ወይም የቱልሳ ህጻናት እና ቤተሰብ ኤጀንሲ ተወካይ የሚከታተልበት ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ሰው በቃለመጠይቅዎ ላይ መቅረብ አይችልም፡፡

4.2.2 ከእርስዎ ጋር ቃለመጠይቅዎ ላይ የሚገኘው ሰው ለእርስዎ ማንኛውንም ጥያቄ መመለስ አይችልም፡፡

4.2.3 የህግ ተወካይ ይዞ መቅረብ ከፈለጉ እርሱ ወይም እርሷ ቃለመጠይቁን እንዲታዘቡ ይፈቀድለታል/ላታል፡፡ የህግ ተወካይዎ በቃለመጠይቁ መጀመሪያና መጨረሻ ላይ አስፈላጊ ነው ብለው ያሉትን ማንኛውም ነጥቦች እንዲያስቀምጡ ዕድል ይሰጣችዋል፡፡ በእርስዎ ቦታ ሆኖ ማንኛውንም ጥያቄ መመለስ አይችልም/አትችልም፡፡

## 4.3 በቃለመጠይቁ ላይ መገኘት ካልቻልኩ ወይም ከቀረሁ ምን ይሆናል?

4.3.1 ለምርመራ ሂደቱ በንቃት መተባበር ግዴታ ስላለብዎት ቃለመጠይቆች ለሌላ ጊዜ ይተላለፉ የሚችሉት በህመም ምክንያት በሌላ **የተለየ** ምክንያት ብቻ ነው፡፡ ወደ ቃለመጠይቁ ለመምጣት ችግር ሊገጥምዎት እንደሚችል ካሰቡ **በቻሉት ፍጥነት** ወዲያውኑ ለአይፒኦ ማሳወቅ ይኖርብዎታል፡፡ የቃለመጠይቁ ቀን ከመድረሱ በፊት ስለመታመምዎ ማስረጃ ከሀኪምዎ (ጠቅላላ ሀኪም ወይም አማካሪ) ለአይፒኦ ማቅረብ ይኖርብዎታል፡፡

4.3.2 በተያያዘው ቀን እና ሰዓት በግል ቃለመጠይቅዎ ላይ ሳይገኙ ከቀሩ እና የቀረበትን አሳማኝ ምክንያት ከቃለመጠይቁ ቀን ጀምሮ <u>እስከ 3 የስራ ቀናት ጊዜ ውስጥ</u> ለአይፒኦ ካላቀረቡ በጥበቃ ሂደት ውስጥ እስከዚያ ድረስ ባስገቡት ማመልከቻ ውስጥ ያስቀመጡትን መረጃ መሰረት በማቅረብ አይፒኦ ማማልከቻውን መመርመሩን ይቀጥላል፡፡ በሌላ አባባል እርስዎ በቃለመጠይቅ ላይ ያለብዎትን ጉዳይ የመግለጽ እድልዎን ተነፍገው ለቃለመጠይቅ ቀጠሮ ከመያዙ በፊት በአስገቧቸው ሰነዶች እና መጠይቆች ውስጥ በተካተተው መረጃ መሰረት ማመልከቻዎ የሚመረመር ይሆናል፡፡

## 4.4 በማመልከቻው ሂደት ላይ መተባበር ግዴታ አለብኝ? ሳልተባበር መቅረቴ ምን ያስከትላል?

4.4.1 ለአለም አቀፍ ጥበቃ ባቀረቡት ማመልከቻ ላይ በሚደረገው ምርመራ ላይ በንቃት የመተባበር ግዴታ አለብዎት፡፡

4.4.2 የእርስዎ የመተባበር ግዴታ መጠነ ሰፊ ሲሆን የሚከተሉትን ያካትታል

(i) የእርስዎን ማመልከቻ ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን (ስለማመልከቻዎ ይዘት በተመለከተ በእጅዎ የሚገኘው ሰነዶችና መግለጫዎችን) ሁሉ በተቻለ ፍጥነት ማቅረብና እውነተኛ መሆን፣ እና

(ii) ማመልከቻዎ ሲመረመር እና ማንኛውም ይግባኝ ሲኖር የመተባበር

4.4.3 እንዲሁም በአለም አቀፍ ጥበቃ አዋጅ 2015 የተካተቱትን ሌሎች ሁሉንም ግዴታዎች ማሟላት ይጠበቅቦታል፡፡ ይህን በተመለከተ እባክዎን **ክፍል 8** ይመልከቱ፡፡

4.4.4 በሚኒስቴሩ ሀሳብ እንደሚከተለው ከሆነ፡-

(i) ማመልከቻዎን ለመመርመር የመተባበር ግዴታዎን ያልተወጡ፣ ወይም

(ii) ያለሚንስቴሩ ፈቃድ በስቴት (አየርላንድ) ለቆ የመውጣት ወይም ለቆ ለመውጣት የመሞከር ግዴታዎን የጣሱ፣ ወይም

(iii) በተቻለ ፍጥነት አድራሻውን ወይም የአድራሻዎን ለውጥ በሚንስቴሩ የማሳወቅ ግዴታዎን ያልተወጡ፣ ወይም

(iv) አርሶ፡-

- በስቴት (አየርላንድ) ውስጥ በአንድ በተወሰነ ዲስትሪክት ወይም ቦታ እንዲኖሩ ወይም እንዲቆዩ፣

  እና

- በተወሰነ የጊዜ ልዩነት ውስጥ ለኢምግሬሽን/ፍልሰት መኮንንኑ ወይም በተወሰነ ጋርዳ ሶቻና ሀገር ሪፖርት የማድረግ፣

ግዴታዎን የጣሱ መሆንዎን ካመኑበት ስለዚህ ሁኔታ ሚኒስቴሩ በጽሁፍ ለእርስዎ በማሳወቅ ምላሾን <u>በ 10 የስራ ቀናት ውስጥ</u> እንዲያቀርቡ ይጋብዞዎታል፡፡ ማመልከቻዎን መቀጠል እንደሚፈልጉ እንዲያረጋግጡ የሚጠየቁ ሰሆን የመተባበር ግዴታዎንም እንዲያስታውሱ ይደረጋል፡፡

4.4.5 እርሶ

(ሀ) ምላሽ ሳይሰጡ ከቀሩ

ወይም መልስዎን ተቀባይነት ካገኘ በኋላ፣

(ለ) በጥበቃ ሂደት ውስጥ እየተባበሩ እንዳልሆነ ሚኒስቴሩ ከወሰነ፣

ማመልከቻዎ ከዚያ ቀደም ሲል ባቀረቡት መረጃ መሰረት ይመረመራል፡፡

## 4.5 የግል ቃለመጠይቁን ጨምሮ የምርመራው ዋና ሂደት ምንድን ነው?

4.5.1 አይፒኦ፡-

- <u>በመጀመሪያ</u> የስደተኛ መብት ሊሰጥዎት እንደሚገባ ወይም እንደማይገባ እና የማይገባ ከሆነ ፡
- የንዑስ ጥበቃመብት ሊሰጥዎት እንደሚገባ ወይም እንደማይገባ
  ለማረጋገጥ የእርስዎን የአለም ጥበቃ ማመልከቻ ይመረምራል፡፡

4.5.2 ሂደቱ በመደበኛነት የሚጠይቀው

- የግል ቃለመጠይቅ፣
- በጽሁፍ ወይም በቃለመጠይቅ ወቅት የሰጧቸውን መረጃ ሁሉ በመጨመር የእርስዎን ማመልከቻ መመርመር እና
- በምርመራው ውጤቶች ላይ ሪፖርት ማዘጋጀትን ይጠይቃል፣ እንዲሁም ይህ ሪፖርት እርስዎ በማንኛውም  የአለም አቀፍ  ጥበቃ መብት ለማግኘት ብቁ እንደሆኑ ወይም እንዳልሆኑ  የሚያሳዩ ግኝቶችና የውሳኔ ሃሳቦችን ያካትታል፡፡

### የግል ቃለመጠይቅ

4.5.3 የግል ቃለ መጠይቅ አላማው ለአለም አቀፍ ጥበቃ ላቀረቡት ጥያቄ ዝርዝር መረጃዎችን ለመቀበል ነው፡፡ ባል/ሚስት በመሰረቱ በተናጠል ቃለመጠይቅ ይደረግላቸዋል፡፡

4.5.4 በቃለመጠይቅ ወቅት፡-

(i) አለም አቀፍ ጥበቃ ለምን እየጠየቁ እንዳለ በግልጽና በአጭሩ ማስረዳት፣

(ii) ለጥገኞችዎ ለምን አለም አቀፍ ጥበቃ እየጠየቁ እንዳለ በግልጽና በአጭሩ ማስረዳት፣

(iii) በእርስዎ የተለየ ሁኔታ እና በጥገኞችዎ ሁኔታ አስፈላጊ የሆኑ ዝርዝር መረጃዎችን እና ሰነዶችን በተለይም እርስዎና ጥገኞችዎ ወደ መጡበት ሀገር/ቀድመው ይኖሩበት የነበረው ሀገር መመለስ ለምን እንደማትችሉ በተመለከተ ያሉትን መረጃዎች ማቅረብ ይኖርብዎታል፡፡

4.5.5 ሙሉ በሙሉ ለመተባበርና እውነት የመናገር ግዴታ አለብዎት ይህን ካላደረጉ እንዳይታመኑ የሚያደርግ ሲሆን **በማመልከቻዎ ምርመራ ላይ እንዳልተባበሩ ተደርገው መወሰድ ያስከትላል (ከላይ አንቀጽ 4.4.4 እና 4.4.5ን ይመልከቱ)፡፡**

4.5.6 ቃለመጠይቅ የሚያደርግልዎት ሰው አስፈላጊ ሆነ ከታየው በማመልከቻዎ ውስጥ የተካተቱትን ጥገኞች ቃለመጠይቅ ሊያደርግ ይችላል፡፡

4.5.7 አግባብነት ያለው መግባባት እንዲኖር ለማስቻል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እና ሲቻል ቃለመጠይቁ በአስተርጓሚ እገዛ ይካሄዳል፡፡

4.5.8 አስተርጓሚው የቃለመጠይቁን ሚስጥራዊነት የመጠበቅ እና ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ያገኘውን ማንኛውንም መረጃ ለማንኛውም ሰው ያለመግለጽ ፣ያለመወያየት፣ ይፋ አለማድረግ እና አሳልፎ ያለመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

4.5.9 እርስዎ ቃለመጠይቅ የሚደረግልዎት አለም አቀፍ ጥበቃን የሚጠይቁ ሰዎችን ቃለመጠይቅ በማድረግ ስልጠና በወሰደ ቃለመጠይቅ አድራጊ ሲሆን እርሱም የመጡበት ሀገር/ቀድመው ይኖሩበት የነበረው ሀገርዎ ዝርዝር መረጃ ያለው ይሆናል፡፡

4.5.10 የተጻፈ/የታተመ የቃለመጠይቁ ቅጂ በቃለመጠይቅ አድራጊ እጅ ይቀመጣል፡፡ መዝገቡንም የመከለስ እድል የሚኖርዎት ሲሆን የእርስዎ ቃለመጠይቅ ትክክለኛ መረጃ መሆኑን ለማረጋገጥ እያንዳንዱ ገጽ ላይ እንዲፈርሙ ይጠየቃሉ፡፡ **በዚህ በተጻፈ ወይም በታተመ መረጃ ውስጥ ትክክል ያልሆነ ነገር መኖሩን ካመኑበት በቀጥታ ለቃለመጠይቅ አድራጊው ሲያሳውቁ በቃለመጠይቁ ወቅት እንዲያስረዱ እድል ይሰጥዎታል፡፡**

4.5.11 ማመልከቻዎን ለመመርመር አስፈላጊ የሆነ ማንኛውም ጉዳይ ጋር በተያያዘ በጽሁፍ ለአይፒኦ ማቅረብ ይችላሉ፡፡ ጉዳዩ የሚመለከተው ማንኛውም ሌላ ሰው ዩኤንኤችሲአር ሊፈቅድ በሚችለው መልኩ እንዲ ሊያደርግ ይችላል፡፡ እንዲህ አይነቱ ማስተካከያ ከቃለመጠይቁ በፊት መደረጋቸው አስፈላጊ ነው፡፡ ቃለመጠይቅ ከእርስዎ ጋር በሚደረግበት ጊዜ ሆነ ከዚያ በፊት የተደረጉትን እንዲህ አይነት ማስተካከያዎችን ሪፖርቱ ከመጠናቀቁ በፊት ከቀረቡ አይፒኦ ግምት ውስጥ ያስገባችዋል፡፡

4.5.12 የግል ቃለ መጠይቅ የአለም አቀፍ ጥበቃ መኮንኑ

(i) ያለው ማስረጃ አመልካቹ የስደተኛ ማረጋገጫ ሊሰጠው የሚገባ ሰው መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን፣

(ii) አመልካች ዕድሜው ከ18 በታች ሆኖ ዕድሜው ወጣት እና ዝቅተኛ የብስለት ደረጃ ላይ ያለ በመሆኑ ቃለመጠይቅ ቢደረግለት ለምርመራው ፋይዳ እንደማይኖረው፣ ወይም

(iii) ከደረሰበት አስቸጋሪ ሁኔታ እና ከቁጥጥሩ ውጪ በሆነ ችግር ምክንያት አመልካቹ ቃለመጠይቅ ለመደረግ ብቁ ያልሆነ ወይም የማይችል መሆኑን

ካመነበት ቃለመጠይቁ ሊቀር ይችላል፡፡

**ማመልከቻዎን ስለመመርመር እና ምክረ ሃሳብ ስለማዘጋጀት**
**sከቃለመጠይቁ በኋላ ምን ይመጣል?**

4.6.1 አይፒኦ በአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ውስጥ ያሉትን አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን ግምት ወስጥ በማስገባት በዚያው መሰረት ምክረ ሃሳብ ያዘጋጃል፡፡

## 4.7 የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ላይ ሊያመጣቸው የሚችሉ ውጤቶች ምንድን ናቸው?

4.7.1 የአለም አቀፍ ጥበቃ መኮንኑ ለአለም አቀፍ ጥበቃ ባቀረቡት ማመልከቻ ላይ የውሳኔ ሃሳብ የያዘ የጸሁፍ ሪፖርት ያቀርባል፡፡ የውሳኔ ሃሳቡም ከሚከተሉት አንዱ ይሆናል፡-

(i) የስደተኛ ማረጋገጫ ሊሰጥዎት እንደሚገባ፣

(ii) የስደተኛ ማረጋገጫ ሊሰጥዎት እንደማይገባ ነገር ግን የድጎማ ጥበቃና ማረጋገጫ ሊሰጥዎት እንደሚገባ፣ ወይም

(iii) የስደተኛ ማረጋገጫ ሆነ የንዑስ ጥበቃማረጋገጫ ሊሰጥዎት እንደማይገባ፡፡

4.7.2 የውሳኔ ሃሳቡ የስደተኛ ማረጋገጫ ሆነ የንዑስ ጥበቃማረጋገጫ ሊሰጥዎት እንደማይገባ የሚገልጽ ከሆነ የአለም አቀፍ ጥበቃ መኮንኑ ሪፖርት ከሚከተሉት አንዱ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ግኝቶችን ሊያካትት ይችላል፡-

(i) ማመልከቻዎ ውስጥ አግባብነት የሌላቸው ጉዳዮች ብቻ የተካተቱ መሆኑን ወይም መረጃዎቹ ለአለም አቀፍ ጥበቃ ብቃትዎ አስፈላጊነታቸው ዝቅተኛ መሆኑን፣

(ii) ማመልከቻዎ ለአለም አቀፍ ጥበቃ ብቁ እንዲሆን በግልጽ የማያሳምኑ ቅደም ተከተላቸው የተዘባ፣ እርስ በራሳቸው የሚጋጩ ፣ሊሆኑ የማይችሉ ወይም በቂ ያልሆኑ ምክንያቶች ያቀረቡ መሆኑን፣

(iii) እድሉ ከተሰጥዎት በኋላ ማቅረብ በሚገባዎት ጊዜ ውስጥ ያለበቂ ምክንያት ማመልከቻዎን ሳያቀርቡ የቀሩ መሆኑን፣

(iv) ወደ መጡበት ሀገር/ቀድመው ይኖሩበት የነበረው ሀገርዎ ጥበቃ ስላለሎዎት የአለም አቀፍ ጥበቃ የማያስፈልግዎ መሆኑን፣

(v) ወደ መጡበት ሀገር/ቀድመው ይኖሩበት የነበረው ሀገር ደህንነቱ የተጠበቀ ሀገር በመሆኑ፡፡

ሪፖርት ውስጥ ከላይ የተቀመጡት ግኝቶች መካከል አንዱ ከተካተተ ለአይፒኤሴቲ ይግባኝ በማቅረብ አጭር ጊዜ ውስጥ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ በይግባኝ ሂደት ላይ መረጃ ማግኘት **ክፍል 5** ይመልከቱ፡፡

4.7.3 እንደ አንድ ሂደት አካል ለስደተኛ ወይም ለንዑስ ጥበቃ ብቁ አልመሆንዎ ከተረጋገጠ ሚንስቴሩ በስቴት (አየርላንድ) ግዛት ውስጥ እንዲቆዩ ፈቃድ እንዲሰጥዎ ማንኛውም ምክንያት መኖሩን እና አለመኖሩን ግምት ውስጥ ያስገባል፡፡ እባክዎን **አንቀጽ 1.6** እና **ክፍል 13** ይመልከቱ ፡፡

4.7.4 ሚኒስቴሩ በተመዘገበ ደብዳቤ አማካይነት ለእርስዎና ለህግ ተወካይዎ (የሚታወቅ ከሆነ) ስለአለም አቀፍ ጥበቃ መኮንኑ የውሳኔ ሃሳብ ያሳውቃችኋል፡፡ የወሳኔ ሃሳቡ የስደተኛ ደረጃ ይሰጥዎ የሚል ከሆነ ስለዚያው ጉዳይ ሁኔታ እንዲያውቁ ይደረጋሉ፡፡

የስደተኛ የንዑስ ጥበቃከተከለከሉ፡-

(i) ምክረ ሃሳቡ ምክንያቶች መግለጫ፣

(ii) ምክረ ሃሳቡን የያዘው ሪፖርት ቅጂ፣ እና

(iii) በዚህ ምክረ ሃሳብ ላይ ለአይፒኤቲ ይግባኝ ማለት ስለሚችሉበት መረጃ ይላክልዎታል፡፡

4.7.5 ለአለም አቀፍ ጥበቃ ብቁ እንዳልሆኑ ከተረጋገጠ ሚንስቴሩ በሌሎች ምክንያት ምክንያቶቹን በመግለጽ በግዛቱ ውስጥ እንዲቆዩ ፈቃድ ለመስጠት የወሰነ ስለመሆን አለመሆን ውሳኔ ይሰጥዎታል፡፡

4.7.6 የአለም አቀፍ ጥበቃ እዳይሰጥዎ (የስደተኛ ደረጃ ወይም የስደተኛ እና የንዑስ ጥበቃ ሁለቱንም ) በተሰጠው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ለአይፒኤቲ ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ፡፡ አይፒኤቲ በይግባኝዎ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ እና ለዚያም የሚሰጣቸው ምክንያቶች ለእርስዎና ለህግ ተወካይዎ (የሚታወቅ ከሆነ) ይደርስዎታል፡፡

4.7.7 <u>ሚኒስቴሩ በሀገር ውስጥ እንዳይቆዩ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ መጠየቅ አይችልም</u>፡፡

4.7.8 የአለም አቀፍ ጥበቃ እንዳይሰጥዎ በተላለፈ የውሳኔ ሃሳብ ላይ ይግባን ከጠየቁ እና አይፒኤቲ የውሳኔ ሃሳቡን ቃጸደቀው ስለእርስዎ ሁኔታ ለውጥ ማንኛውም አዲስ መረጃ (ለውሳኔ አስፈላጊ የሆነ) የመጀመሪያው ወሳኔ ከተላለፈ በኋላ ካቀረቡ ሚኒስቴሩ እዚህ ሀገር ውስጥ እንዳይቆዩ የሰጠውን ውሳኔ ይከልሳል (**አንቀጽ 13.5** ይመልከቱ)፡፡

## 4.8 ለአለም አቀፍ ጥበቃ ባቀረብኩት ማመልከቻ ላይ የውሳኔ ሃሳብ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ካልደረሰኝ ምን ይፈጠራል?

4.8.1 ለአለም አቀፍ ጥበቃ ባቀረብኩት ማመልከቻ ላይ የውሳኔ ሃለአለም አቀፍ ጥበቃ ባቀረቡት ማመልከቻ ላይ የውሳኔ ሃሳብ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ካልደረስዎ ሚኒስቴሩ እርስዎ ጥያቄ ሲያቀርቡለት የውሳኔ ሃሳብ የሚቀርብለትን ግምታዊ ጊዜ በተመለከተ መረጃ ይሰጥዎታል፡፡ ነገር ግን ይህ የጊዜ ግምት አይፒኦ የውሳኔ ሃሳቡን ማቅረብ ያለበት አስገዳጅ የጊዜ ገደብ አይደለም፡፡

**ክፍል 5**
**ይግባኝና የአለም አቀፍ ጥበቃ**

## 5.1 እኔ አለም አቀፍ ጥበቃ እንዳይሰጠኝ በሚቀርቡት እና በሌሎች የውሳኔ ሃሳቦች ላይ ይግባኝ የመጠየቅ መብት አለኝ?

5.1.1 አዎ፡፡ የስደተኛ ወይም የስደተኛ እና የንዑስ ጥበቃ ለማግኘት ብቁ እንዳልሆኑ የውሳኔ ሃሰባ ከቀረበብዎት በውሳኔ ሃሳቡ ላይ ይግባኝ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

5.1.2 እንዲሁም፣

(i) የጥበቃ ማመልከቻዎ አያስቀርብም፣ ወይም

(ii) ለአለም አቀፍ ጥበቃ ከዚያ በኋላ ማመልከት (ተከታይ ማመልከቻ) የማይፈቀድልዎት ስለመሆኑ

በቀረበ የውሳኔ ሃሳብ ላይ ይግባኝ የመጠየቅ መብት አልዎት፡፡

## 5.2 ይግባኝ እንዴት ነው የማቀርበው?

5.2.1 ለአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኞች ሰሚ ችሎት ይግባኝዎን መላክ ይኖርብዎታል፡፡ የውሳኔ ሀሳቡን ሲቀበሉ መሙላት ያልብዎትን የይግባኝ ቅጽ ይሰጥዎታል

## 5.3 ይግባኝ ለማቅረብ የጊዜ ገደቡ ምን ያህል ነው?

5.3.1 አስፈላጊ የሆነው የጊዜ ገደብ ዝርዝር በሚሰጥዎት የውሳኔ ሃሳብ ውስጥ ይካተታል፡፡

## 5.4 ለይግባኙ የህግ ተወካይ የማቅረብ መብት አለኝ?

5.4.1 አዎ፡፡ ስለይግባኝዎ ከህግ ተወካይዎ ጋር መወያየት አልብዎት፡፡የህግ ተወካይ ከሌልዎት የህግ ድጋፍ ቦርድን ማነጋገር ይችላሉ፡፡ በአማራጭነት በራስዎ ወጪ የግል ጠበቃ እንዲያግዝዎት መቅጠር ይችላሉ፡፡

## 5.5 ይግባኝ በምን ያህል ፍጥነት ሊታይ ይችላል?

5.5.1 ይግባኙ መቼ እንደሚታይ ዝርዝሩን የአለም አቀፍ ይግባኞች ሰሚ ችሎት ይገልጽልዎታል

## 5.6 ስለ ይግባኝ ሂደት የበለጠ መረጃ ከየት ላገኝ እችላለሁ?

5.6.1 ከአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ጋር በተያያዘ የይግባኝ ሂደት መረጃ በተመለከተ በአይፒኤቲ ድረገጽ www.protectionappeals.ie ይገኛል፡፡

## ክፍል 6
## የስደተኛነት ወይም ንዑስ ጥበቃ ማረጋገጫ

### 6.1 የውሳኔ ሃሳብ ከተቀበልኩ በኋላ ምን ይከሰታል?

6.1.1 አይፒኦ እርስዎ የስደተኛ ወይም የንዑስ ጥበቃማረጋገጫ እንዲሰጠው የውሳኔ ሃሳብ ይሰጣል ወይም አይፒኤቲ አይፒኦ የሰጠውን አሉታዊ የውሳኔ ሃሳብ ይሽራል፣ ሚኒስቴሩ በተቻለ መጠን ወዲውኑ እንደተፈጻሚነቱ የስደተኛ ማረጋገጫ ወይም የንዑስ ጥበቃማረጋገጫ ይሰጥዎታል፡፡ ይህም የሚፈጸመው ከዚህ በታች በተቀመጠው **አንቀጽ 6.1.4** መሰረት ይሆናል፡፡

6.1.2 አይፒኦ የማረጋገጫ ቅጽ እንደማይሰጥዎ የውሳኔ ሃሳብ ካቀረበ፣ እና

(i) እርስዎ ይግባኝ ካልጠየቁ፣ ወይም፣

(ii) ይግባን ከጠየቁ እና ሰኬታማ ካልሆኑ፣

ሚኒስቴሩ ምንም አይነት የመግለጫ ቅጽ እዳይሰጥዎ ይከልከላል

6.1.3 እርስዎ የአየርላን ዜግነት ካገኙ የስደተኛ ማረጋገጫ ወይም የንዑስ ጥበቃማረጋገጫ ተፈጻሚነቱ ያበቃል፡፡

6.1.4 ምንም እንከኳን አይፒኦ የውሳኔ ሃሳብ ቢያቀርብም ወይም አይፒኤቲ በይግባኞዎ ላይ ስደተኛ እንደሆኑ ቢወስንም፡-

(i) ለአየርላንድ ሀገር ደህንነት አደገኛ እንደሆኑ የሚያስቆጥር አሳማኝ ምክንያት ካለ፣ ወይም

(ii) በስቴት (አየርላንድ) ወይም ከዚያ ውጪ ከባድ ወንጀል ሰርተው የተፈረድብዎት በመሆንዎ ለስቴት (አየርላንድ) ሀገር ማህበረሰብ አደጋ መሆንዎ ከታመነ ሚኒስቴሩ ማረጋገጫ እንዳይሰጠው ሊከለክል ይችላል፡፡

## ክፍል 7
## የአለም አቀፍ ጥበቃ ካገኙ የሚኖሮት መብት

### 7.1 የአለም አቀፍ ጥበቃ ካገኘው የሚኖሩኝ መብቶች ምንድን ናቸው?

7.1.2 የስደተኛ ወይም የንዑስ ጥበቃ ማረጋገጫ ካገኙ በአለም አቀፍ ጥበቃ አዋጅ 2015 ድንጋጌዎች መሰረት የሚከተሉት መብቶች ይኖርዎታል፡-

(i) በማንኛውም እና በሁሉም ረገድ ከአየርላንድ ዜጋ እኩል እና እንደ ስቴቱ (አየርላንድ) ዜጋ ሁሉ በአየርላን ግዛት ውስጥ ስራ የመፈለግና የመግባት፣ በማንኛውም ስራ ላይ የመሰማራት ፣በማንኛውም ሙያ ፣ንግድ የመሰማራት እና ትምህርትና ስልጠና የማግኘት፣

(ii) ለአየርላንድ ዜጎች ተፈጻሚ በሚሆነው ሁኔታ መሰረት የህክምና እንክብካቤ እና ለአየርላን ዜጎች የተሰጡ የማህበራዊ ጥቅማጥቅሞች መብቶች የማግኘት፣

(iii) በስቴቱ (አየርላንድ) ውስጥ ከሶስት አመት ላላነሰ **የተወሰነ ጊዜ** የመኖርና ይህን በሁኔታዎች መሰረት የሚታደስ ይሆናል፣ እና

(iv) የአየርላንድ ዜጎች በተሰጣቸው መብት መሰረት ከእና ወደ ስቴት (አየርላንድ) የመሄድና ፓስፖርት የማግኘት መብት ይንሮዎታል፡፡

## ክፍል 8
## በአለም አቀፍ ጥበቃ ሂደት ውስጥ ያሎት መብቶችና ግዴታዎች

### 8.1 በአለም አቀፍ ጥበቃ ሂደት ውስጥ ያሉኝ መብቶችና ግዴታዎች ምንድን ናቸው?

8.1.1 የእርስዎ ጉዳይ የተወሰኑ አማራጭ ሁኔታዎች ተፈጻሚ የሚሆንበት (**ክፍል 10** ይመልከቱ) በአውሮፓ ህብረት የደብሊን መመሪያ መሰረት የሚታይ ካልሆነ በስተቀር ለአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካች የሚተበቁ መብቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

(i) ለአለም አቀፍ ጥበቃ ያቀረቡት ማመልከቻ በአይፒኦ እንዲመረመር እና ይግባኝዎ በአይፒኤቲ እንዲታይ ሲባል ወደ ስቴቱ (አየርላንድ) ገብተው እንዲቆዩ በሚኒስቴሩ ፈቃድ ይሰጥዎታል **አንቀጽ 8.1.2** ይመልከቱ፡፡

(ii) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና የሚቻል ሲሆን አግባብነት ያለው መግባባት እንዲኖር በማድረግ አስተርጓሚ የማግኘት መብት፡፡

(iii) ከህግ ድጋፍ ቦርድ የህግ ምክርና ድጋፍ የመጠየቅ መብት፡፡ እንደአማራጭም ከፈለጉ በራስዎ ወጪ የግል የህግ ተወካይ ሊቀጥሩ ይችላሉ፡፡

(iv) ከተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን ጋር የመነጋገር መብት፡፡ ስልካቸውና ኢሜይል አድራሻቸው ዝርዝሩ **በቅጥያው** ተካተዋል፡፡

(v) ከማመልከቻ ዋጋ በተያያዘ ለሚኒስቴሩ ተጨማሪ ማስረጃዎች የማቅረብ መብት አልዎት፡፡ እነዚህ ማስረጃዎች የሚቀርቡት በጹሁፍ መሆን አለበት፡፡

(vi) አርአይኤ የጥበቃ ማመልከቻዎ በሂደት ላይ ሲሆን የተሟላ ማረፊያ ቤት ሊሰጥዎ ይችላል፡፡ ይህንን መብት ተጠቃሚ የሚሆኑት በwww.ria.ie. የሚገኙትን የቤት አጠቃቀም ደንቦች ሲያከብሩ ይሆናል፡፡ የአይአርኤ አድራሻ ዝርዝር **ቅጥያ** ውስጥ ተካተዋል፡፡

(vii) ከማመልከቻዎ ጋር ተያይዘው የቀረቡ ዝርዝሮች ሁሉ በሚስጥርነት ይያዛሉ፡፡ ነገር ግን ጉዳዩ ለሚመለከታቸው እንደ አየርላንድ መንግስት ሚንስቴሮችና ኤጀንሲዎች፣ የሚግሬሽን ባለስልጣናት፣ጋርዳሶሺያ (የአየርላንድ ፖሊስ) እና ለአካባቢ ባለስልጣናት መረጃ ይፋ ሊደረግ ይችላል፡፡ ይህም መረጃ እነዚህ ተቋማት የውጪ ሀገር ዜጎች ወደ ስቴቱ (አየርላንድ) የሚገቡበት እና የሚወጡበትን ህግ ማስተዳደርን ጨምሮ ያላቸውን ተግባር እንዲወጡ ያስችላቸዋል፡፡ የተወሰነ መረጃ በአውሮፓ ህብረት ደብሊን መመሪያ ለሚሰሩ ሌሎች ሀገሮች ሊቀርብ ይችላል፡፡

(viii) ለአለም አቀፍ ጥበቃ ካቀረቡት ማመልከቻ ጋር የተያያዘ ቀጠሮዎችን፣ ቃለመጠይቆችን፣ ወሳኔዎችን እና ሌሎች ማናቸውንም ከዚያ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች እርስዎ በሰጡት አድራሻ አማካይነት በጽሁፍ አይፒኦ፣አይፒኤቲ ወይም ሚኒስቴሩ ያሳውቅዎታል፡፡

8.1.2 የግዛዊ መኖሪያ ምስክር ወረቀትዎ የአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካችነትዎ እስከሚያበቃ ድረስ በአጠቃላይ የሚያገለግል ሲሆን ለምሳሌ ሚንስቴሩ የስደተኛ ወይም የንዑስ ጥበቃማረጋገጫ እንዳይሰጥዎ ሲከለከል ወይም በአውሮፓ ህብረት ደብሊን መመሪያ መሰረት ከስቴቱ (አየርላንድ) በሚዘዋወርበት ጊዜ ፡፡

## 8.2 በአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ሂደት ውስጥ ያሉ ግዴታዎች ምንድን ናቸው?

8.2.1 እንደ አለም አቀፍ ጥበቃ አመልካችነትዎ የሚከተሉት መብቶች ይኖርዎታል፡-

(i) የሀገሪቱን (አየርላንድ) ህጎችን እና ሌሎች ሊጣልብዎት የሚችሉ ሌሎች ማንኛውም ግዴታዎችን የማክበር፡፡

(ii) ማመልከቻዎ ሲመረመርና ይግባኝዎ ሲጣራ ከዚያ ጋር በተያያዘ ለሚጠየቁት ነገር ሙሉ ትብብር ማድረግ፡፡ ይህም ሲባል ማመልከቻውን ለመደገፍ በእጅዎ የሚገኝ ሁሉንም መረጃና ሰነዶች ማቅረብን ያካትታል፡፡

(iii) አድራሻዎን ከለወጡ አዲሱን አድራሻዎን ዝርዝር **ወዲያውኑ በጽሁፍ ለአይፒኦ ማሳወቅ ይኖርብዎታል**፡፡ ይህ ወደሌላ መኖሪያ በቅበላና መስተንግዶ ኤጀንሲ (አርአይኤ) ከተዘዋወሩ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ **ይህንን አለማድረግ ጥፋት ነው**፡፡

(iv) ከአይፒኦ ወይም ከአይፒኤቲ ጋር በሚያደርጓቸው የመልዕክት ልውውጦች ሁሉ በጊዜያዊ መኖሪያ መስክር ወረቀትዎ ላይ የተገለጸውን **ስም፣ አድራሻ ፣ዜግነት እና የመታወቂያ ቁጥር በግልጽ ማመልከት ይኖርብዎታል፡፡**

(v) ማመልከቻዎ እየተመረመረ ባለበት ወቅት ያለ ሚኒስቴሩ ፈቃድ **ስቴቱን (አየርላንድ) መልቀቅ ወይም ለመልቀቅ መሞከር የለብዎትም፡፡** ያለ ሚኒስቴሩ ፈቃድ ስቴቱን (አየርላንድ) መልቀቅ **ጥፋት** ነው፡፡

(vi) **ስራ ለመፈለግ ስራ ለመግባት ወይም ለመቀጠር ወይም ገንዘብ የሚስገኝ ማንኛውም ስራ ፣ ንግድ ወይም ሙያ ላይ ለመሰማራት መብት የልዎትም**፡፡ በስራ ሆነ በቅጥር ውስጥ መሰማራት **ጥፋት** ነው፡፡

(vii) እርስዎ ወይም የእርስዎ የህግ ተወካይ በአይፒኦ እና አይፒኤቲ የሚሰጥዎትን **ሁሉንም የሰነዶች ቅጂ** መያዝ አለባችሁ፡፡

(viii) በስቴቱ (አየርላንድ) ውስጥ **በተወሰነ ቦታ እንዲቆዩ ወይም እንዲኖሩ ሊደረጉ ይችላሉ፡፡** ይህንን አለማድረግ **ጥፋት** ነው፡፡

(ix) **በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ** ለፍልሰት መኮንን ወይም ለተወሰነ ገራዳ ሶርሺያ ሶቼና (የአየርላንድ ፖሊስ) ሪፖርት እንዲያደርጉ ሊጠየቁ ይችላሉ፡፡ ይህንን አለማድረግ **ጥፋት** ነው፡፡

(x) ከማመልከቻዎ ጋር በተያያዘ በሚሰጡት መረጃ ሁሉ **እውነተኛ** መሆን አልብዎት ይህንን አለማድረግ **ጥፋት** ነው፡፡

(xi) በመጠይቅዎ ውስጥ የመቆየት ፈቃድ ለመስጠት ለሚኒስቴሩ ውሳኔ አስፈላጊ ሊሆን የሚችል ማንኛውንም መረጃ ማካተት አለብዎት ፡፡ እንዲሁም ማመልከቻዎን ካስገቡበት ጊዜ እስከ የጥበቃ ማመልከቻዎን ሪፖርት ዝግጅት ድረስ እንዲቆዩ ፈቃድ በመስጠት ወይም ባለመስጠት የሚኑስቴሩ ውሳኔ አስፈላጊ የሆነ ማንኛውንም መረጃ ማቅረብ ይችላሉ፡፡ ለሚኒስቴሩ ውሳኔ አስፈላጊ የሆነ ማንኛውንም የእርስዎን ሁኔታ ለውጥ መረጃ ወዲያውኑ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ ይኖርብዎታል፡፡ የመቆየት ፈቃድ በተመለከተ መረጃ **በክፍል 13** ውስጥ ይገኛል፡፡

(xii) በእርስዎ እጅ ያለን ወይም የሚያገኙትን አስፈላጊውን መረጃ በተቻለ ፍጥነት ለአይፒኦ ወይም ለአይፒኤቲ ማቅረብ ይኖርብዎታል፡፡

**<u>ጠቃሚ ማስታወሻ</u>**

**8.2.2 ስለ ህግ ተወካይዎ( ስም፣አድራሻ፣ስልክ ቁጥር ወዘተ) እና ስለህግ ተወካይ ማንኛውም ለውጥ ዝርዝር በተቻለ ፍጥነት ወዲያውኑ** ለአይፒኦ ወይም ለአይፒኤቲ ( እንደአግባብነቱ) ማቅረብ ይኖርብዎታል፡፡ ይህንን ካለደረጉ ከህግ ተወካይዎ የሚያገኙትን የህግ ምክርና ድጋፍ ለአለም አቀፍ ጥበቃ ባቀረቡት ማመልከቻ ላይ በሚሰጡት ውሳኔዎች እና መልዕክቶች ድጋፍ እንዳያገኙ ሊያደርጎት ይችላል፡፡

## ክፍል 9
## አብሯቸው ሰው የሌለ ሕጻናት

### 9.1 እኔ አብሮኝ ሰው እንደሌለኝ ህጻን ሆኜ የአለም አቀፍ ጥበቃ ባመለከት ምን ይፈጠራል?

9.1.1 እርስዎ ህጻን መሆንዎ (ከ18 ዓመት በታች) ከታመነ እና ለእንክብካቤዎ እና ጥበቃ ኃላፊነት የሚወስድ ሰው አብርዎት ከሌለ ወደ ቱስላ -ህጻናትና ቤተሰብ ኤጀንሲ ይላካሉ፡፡

9.1.2 በአይፒኦ የሚደረግ የዕድሜ መመዘኛ ቃለመጠይቅ እንዲያደርጉ ሊጠየቁ ይችላሉ፡፡ የዕድሜ ምርመራ ቃለመጠይቅዎ በእርስዎ ጉዞ አካሄድ፣ ቤተሰቦችዎ ስላሉበት ቦታ ፣የትምህርት ደረጃ እና የብስለት ሁኔታ ላይ አንዳንድ መሰረታዊ ሀቆችን ለመለየት የተዘጋጀ ነው፡፡ ቃለመጠይቁን የሚያደርገው መኮንን ዕድሜው ከ 18 ዓመት በታች መሆን አለመሆኑን በመወሰን አስፈላጊ ከሆነ **ወደ ቱስላ-ህጻናትና ቤተሰብ ኤጀንሲ ድጋፍ እንዲላኩ ያደርጋል**፡፡

9.1.3 ወደ ቱስላ-ህጻናትና ቤተሰብ ኤጀንሲ ከተላኩ ኤጀንሲው ኃላፊነት በመውሰድ ለአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቱ የእርስዎን ጥቅም የሚያስጠብቅ መሆን አለመሆኑን ወይም ሌሎች እንደ ቤተሰብ ቅልቅል ወይም ቤተሰብ ፍለጋ ተፈጻሚ ሊሆኑ የሚችሉ አማራጮች መኖራቸው ይወስናል፡፡

### 9.2 ቱስላ - የህጻናትና ቤተሰብ ኤጀንሲ ለእኔ የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ካስገባልኝ የሚኖረው ሂደት ምንድን ነው?

9.2.1 ቱስላ - የህጻናትና ቤተሰብ ኤጀንሲ ለእኔ የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ካስገባልዎት በሚቀርብለት የህግ ምክር ውስጥ በሚካተተው መረጃ መሰረት ለእርስዎ በሚያመቾት መሰረት በእርስዎ ቦታ ሆነው እንዲአይነቱን ማመልከቻ የሚያቀርብ የቱስላ ህጻናት ና ቤተሰብ ኤጀንሲ ሰራተኛ ወይም ሌላ ሰው ተሰይሞ በቃለመጠይቁና በምርመራ ሂደት እንዲያግዝዎ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

### 9.3 ከ18 አመት በታች የሆነ ህጻን ወደ ህግ ድጋፍ ቦርድ ለመምራት ያለው ሂደት ምንድን ነው?

10 ቱስላ የህጻናትና የቤተሰብ ኤጀንሲ ለእርስዎ የህግ ተወካይ ለማመቻቸት የህገፍ ድጋፍ ቦርድን ማነጋገር ይችላል፡፡ ወደ ቃለመጠይቅዎ ከእርስዎ ጋር እንዲሄድ ለማድረግ ከቱስላ ህጻናትና ቤተሰብ ኤጀንሲ ጋር ልዩ ድርድር ይመቻቻል፡፡

## ክፍል 10
## ኢዩ (አውሮፓ ህብረት) ደብሊን ደንብ

### 10.1 የአውሮፓ ህብረት ደብሊን ደንብ ምንድን ነው?

10.1.1 የአውሮፓ ህብረት ደብሊን ደንብ አባል በሆኑ ሀገራት በአንዱ በሌላ ሶስተኛ ሀገር ዜጋ ወይም ዜግነት በሌለው ግለሰብ የቀረበ የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ የሚመረምር ሀገር መንግስት ምርመራውን የሚያካሄድበት መስፈርት እና ዘዴዎች በተመለከተ የህግ አግባቦችን እና የአካሄድ ደንቦችን ይደነግጋል፡፡

10.1.2 በአይፒኦ የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ካቀረቡ በደብሊን ሂደት ላይ ተጨማሪ መረጃ ይሰጥዎታል፡፡

10.1.3 እርስዎ በአውሮፓ ህብረት ደብሊን ደንብ በድንጋጌዎች መሰረት ከቀረቡ የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዎ እዛው እንዲመረመር ወደ ሌላ አባል ሀገር ሊዘዋወሩ ይችላሉ፡፡

## ክፍል 11
## በፈቃደኝነት የመመለስ አማራጮች

### 11.1 ወደ መጣሁበት ሀገር/ቀድመው እኖርበት ወደ ነበረው ሀገር በፍቃደኝነት የመመለስ አማራጭ አለኝ?

11.1.1 የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዎ እየተመረመረ ባለበት ጊዜ ወይም ማመልከቻዎ ውድቅ ከተደረገ  በኋላ በማንኛውም ጊዜ በፈቃደኝነት ወደ መጡበት ሀገር/ቀድመው ይኖሩበት የነበረው ሀገር የመመለስ አማራጭ ክፍት ሆኖ ይጠብቅዎታል፡፡ የጥበቃ ማመልከቻዎ እንዲወጣ ከተደረገ በዛ ደረጃ ላይ በፍቃደኝነት ወደ መጡበት ሀገር/ቀድመው ይኖሩበት የነበረው ሀገር የመመለስ አማራጭ ይኖርዎታል፡፡

11.1.2 ሚኒስቴሩ የእርስዎን አለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ወድቅ ማድረጉን ስለውሳኔው ካሳወቅዎት ስለ በፍቃደኝነት ወደ መጡበት ሀገር የመመለስ አማራጭ በግልጽ እንዲያውቁ ይደረጋል፡፡ በዚያ ደረጃ ላይ ይህን አማራጭ እንዲኖር ለማድረግ ሚኒስቴሩ ካሳወቅዎት ቀን ጀምሮ በ5 ቀናት ጊዜ ወስጥ ለሚኒስቴሩ በጹሁፍ ማሳወቅ ይኖርብዎታል፡፡ የውሳኔ ደብዳቤው በፍቃደኝነት ወደ መጡበት ሀገር/ቀድመው ይኖሩበት የነበረው ሀገር መመለስዎን በማመቻቸት ማንን ማነጋገር እንዳልብዎት ዝርዝሩን አካቷል፡፡

11.1.3 ወደ መጡበት ሀገር/ቀድመው ይኖሩበት የነበረው ሀገር በፈቃደኝነት ለመመለስ ከወሰኑ ምክርና  ፈቃድ አለም አቀፍ የስደት ድርጅት  ማግኘት ይችላሉ፡፡ ስለ አድራሻቸው ዝርዝር እባክዎን **ቅጥያን** ይመልከቱ ፡፡

11.1.4 አይኦኤም አስፈላጊውን የመጓጓዣ ሰነድ እንዲያገኙ እና ከአየርላንድ ወደ መጡበት ሀገር የሚመለሱበትን የገንዘብ ወጪ በመሸፈን ሊረዳዎት ይችላል፡፡ በተጨማሪም የገቢ ማስገኛ ስራ ወጪያቸውን እንደትምህርት ፤የሙያ ስልጠና እና/ወይም የስራ መቋቋሚያ የሚሆን ትንሽ የማገገሚያ የገንዘብ ስጦታም ይኖራል፡፡

11.1.5 ወደ መጡበት ሀገር/ቀድመው ይኖሩበት የነበረው ሀገር በፍቃደኝነት የመመለስ አማራጭ ላለመቀበል ከመረጡ ሚኒስቴሩ ተገደው ወደ መጡበት ሀገር እንዲመለሱ ትዕዛዝ ሊሰጥና ከዚህ ስቴት (አየርላንድ) እንዲወጡ ሁኔታዎች ይመቻቹ ይችላሉ፡፡ ከሀገር እንዲወጡ የተሰጠውን ትዕዛዝ ካላከበሩ ስቴት (አየርላንድ) ለመቆየት ህጋዊ ምክንያት አይኖርዎትም፡፡

11.1.6 የፍትህና እኩልነት ሚኒስቴርም ወደ መጡበት ሀገር/ቀድመው ይኖሩበት የነበረው ሀገር በፍቃደኝነት ለመመለስ የሚፈልጉ እና ድጋፍ የሚጠይቁ ሰዎችን አስተዳደራዊና ሌሎች ድጋፎችን በማቅረብ ቀጥተኛ እገዛ ያደርጋል፡፡

11.1.7 በፍቃደኝነት ወደ መጡበት ሀገር/ቀድመው ይኖሩበት የነበረው ሀገር የመመለስ አማራጭ መኖሩ እንዲህአይነቱ እድል ለወደፊት በህጋዊ መንገድ ወደ ስቴቱ (አየርላንድ) ለመመለስ ያስችሎታል በሌላ በኩል ደግሞ ከሀገር ተገዶ አንዲወጣ ትዕዛዝ የተላለፈበት ሰው በህጉ ከስቴቱ (አየርላንድ) እንዲወጣ የሚገደድ እና በኋላ (ላይ ትዕዛዙን ካልተሸረ  በስተቀር)

ከስቴቱ (አየርላንድ) ውጪ እንዲቆይ ይደረጋል፡፡

# ክፍል 12
# ሌላ መረጃ

## 12.1. ለአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ቅድሚያ ለመስጠት ያሉ ሂደቶች ምንድን ናቸው?

12.1.1 ሚኒስቴሩ ከአለም አቀፍጥበቃ ማመልቻዎች አንጻር ፍታሃዊና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነበት ለማንኛውም የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ቅድሚያ ሊሰጥ ይችላል ፡፡

12.1.2 ሚኒስቴሩ ቅድሚያ ለመስጠት የሚከተሉትን ነጥቦች ግምት ውስጥ ያስባል፡-

(i) አመልካቹ የመታወቂያ ሰነድ መያዝ አለመያዙን እና ካልያዘ አመልካቹ እንዲህ አይነቱን ሰነድ ለምን እንዳልያዘ አሳማኝ ገለጻ ማድረግ አለማድረጉን፣

(ii) አመልካቹ ከመጡበት ሀገር/ቀድመው ይኖሩበት የነበረው ሀገር ከወጣበት/ከወጣችበት ጊዜ ጀምሮ ያረፈበት የመጀመሪያ ሰላማዊ ሀገር ስቴቱ (አየርላንድ) መሆኑን ለማረጋገጥ አሳማኝ ገለጻ መድረግ አለማድረጉን/አለማድረጓን፣

(iii) አመልካቹ ወደ ስቴት (አየርላንድ) ለመምጣት እንዴት እንደተጓዘ/እንደተጓዘች እንዴት እንደደረሰ የተሟላላ እና እውነተኛ መግለጫ ማቅረብ አለማቅረቡን፡፡

(iv) አመልካቹ ከስቴት (አየርላንድ) ድንበር ውጪ ማመልከቻ አቅረቦ ከሆነ፣ አመልካቹ ለአለም አቀፍ ጥበቃ ለምን እንዳላመለከተ/እንዳላመለከተች በቂ ምክንያት አቅርቦ እንደሆነ፣ የጥበቃ ማመልከቻ ለምን እንዳቀረበ ወይም አለማቅረቡን ወይም እንደ ሁኔታው በስደተኞች አዋጅ ቁጥር 1996 መሰረት ማመልከቻው አመልካቹ ወደ ስቴት (አየርላንድ) ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ በተከሰቱት ሁኔታዎች ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ማመልከቻ ወዲያውኑ እንደገባ በክፍል 8 መሰረት ለምን እንዳላቀረበ አሳማኝ ምክንያት ማቅረብ አለማቅረቡ፡፡

(v) አመልካቹ የያዛቸው ሰነዶች የሀሰተኛ፣ የተበላሸ ወይም ለመለየት የሚያስቸግር ከሆነ እንዲለመሆኑ አሳማኝ ምክንያት ማቅረብ አለማቅረቡ ፡፡

(vi) አመልካች ማመልከቻውን ለመደገፍ ሆን ብሎ የእውሸት ማስረጃ ወይም በጽሁፍም ሆነ በቃል  የውሸት መረጃ ማቅረብ አለመቅረቡ፡፡

(vii) አመልካቹ ከስቴት (አየርላንድ) እንዲወጣ ሀሳብ መቅረቡን ተከትሎ ማመልከቻ ያለበቂ ምክንያት ማቅረብ አለማቅረቡን፡፡

(viii) አመልካቹ ለጥበቃ ሂደቱ ተባባሪ መሆኑና/አለመሆኗ፡፡

(ix) አመልካቹ ቱስላ የህጻናትና ቤተሰብ ኤጀንሲ እንክብካቤና ጥበቃ የሚያደርግለት ሰው መሆን አለመሆኑ፡፡

(x) አመልካቹ ወደ ስቴቱ (አየርላንድ) ገብቶ ከመቆየት ጋር በተያያዘ የተወሰኑ መስፈርቶችን ያለበቂ ምክንያት ሚሟላት መቻል አለማቻሉን፡፡

## 12.2 ለአለም አቀፍ ጥበቃ ጽ/ቤት ያቀረብኩት መረጃ ምን ይደረጋል?

12.2.1 ስለ ግል መረጃዎ ዝርዝር ለኤፒአ ተሰጥቶ ጸ/ቤቱ ዝርዝሩን በሚስጥርና በአግባቡ የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡

12.2.2 እርስዎ በእርስዎ ላይ የሚያዘውን መረጃ በመረጃ ጥበቃ አዋጅ 1988 እና 2003 ስር በተቀመጠው መብትዎ መሰረት ትክክለኛ መረጃ ማስገባትና የተሳሳተው የመሰረዝ መብት ይኖርብዎታል፡፡

12.2.3 በአየርላንድ ዜግነት መስጠትና ፍልሰት አገልግሎት የተያዘ <u>የግል መረጃ</u> ጋር የሚገናኝ መዝገብ ከተወሰኑት ማግለያዎች በስተቀር በ2014 የወጣው የመረጃ ነጻነት ስር የሚታዩ ናቸው ፡፡

12.2.4 በ2014 የወጣው የመረጃ ነጻነት አዋጅ እያንዳንዱ ሰው፡-

(i) በመንግስት አካላት የተያያዙ መረጃዎችን ማግኘት እንዲችል፡፡

(ii) ስለራሱ የተያዘ ህጋዊ መረጃ ያልተሟላ የተሳሳተ እና አሳሳች ከሆነ በራሱ እንዲስተካከል ማድረግ እንዲችል፡፡

(iii) እራሱን በሚነዳ ውሳኔ ላይ የምክንያት ማብራሪያ የማግኘት ህጋዊ መብት ተጠቃሚ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

12.2.5 የ 2014 አዋጅ የህብረተሰቡ አባላት እስከታቸለው ከፍተኛ ደረጃ ድረስ የመንግስትን ጥቅም ማስከበር እና የግለሰቦችን የግል መብት በማይነካ መልኩ ይፋዊ መረጃዎችን እንዲያገኙ ይደነግጋል፡፡

12.2.6 እባክዎን በመረጃ ጥበቃ ላይ የበለጠ መረጃ ለማግኘት የአይፒአ ድህረ ገፅን www.ipo.gov.ie ይጐብኙ፡፡

## ክፍል 13
## የመቆየት ፈቃድ

### 13.1 የመቆየት ፈቃድ ለማግኘት እዴት ነው የማመለከተው?

13.1.1 ለአለማቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ሲያስገቡ በዛኑ ሰዓት ምን አልባት የስደተኛ መብት ወይም የንኡስ ጥበቃ ሳይሰጥዎ ከቀረ በሀገር ውሰጥ ስለመቆየትዎ ፈቃድ ለመስጠት ወይም ላለመስጠት ሚኒስቴሩ ለሚሰጠው ውሣኔ አስፈላጊ የሆነ በእጅዎ የሚገኝ ማንኛውንም መረጃ ማቅረብ ይኖርብዎታል፡፡ ሚኒስቴሩ ግምት ውስጥ እንዲያስገባው የሚፈልጉት ማንኛውም ነገር ካለ በተቻለ ፍጥነት ወዲያውኑ ይህንኑ ለአይፒኦ ማረጋገጥ ይኖርብዎታል፡፡

13.1.2 በአለማቀፍ ጥበቃ መጠይቅዎ ውስጥ አግባብነት ባለው ቦታ ላይ ይህንን መረጃ መሙላት ይኖርብዎታል፡፡ ሰነዶችን (ለምሳሌ ልደት ምስክር ወረቀት፣ የጋብቻ ምስክር ወረቀት፣ የባህሪ ምስክር ወረቀት፣ ማረጋገጫዎች ወይም የትምህርት ደረጃ ማስረጃዎች ወዘተ) የመሳሰሉ እርስዎ አስፈላጊ ናቸው ብለው ያመኑባቸውን ደጋፊ ሰነዶች አብረው ማቅረብ ይኖርብዎታል፡፡ በወቅቱ እነዚህ ሰነዶች በእጅዎ ከሌሉ በኋላ አይፒኦ ሰለ እርስዎ የአለማቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ሪፖርት ለሚኒስቴሩ እስከሚያዘጋጅ ድረስ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

13.1.3 በተጨማሪም፣ ምንም አይነት ለውጥ ካለና የሁኔታውን ለውጥ እርስዎ ሀገር ውስጥ እንዲቆዩ ሚኒስቴሩ ለሚሰጠው ውሣኔ አስፈላጊ የሚሆን ከሆነ ለአይፒኦ ወቅታዊ መረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

13.1.4 እባክዎን በአይፒኦ የሚደረገው ቃለመጠየቅ በአርስዎ የአለማቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ምርመራ የሚመራ እንጂ በሀገር ውሰጥ እንዲቆዩ የተሰጠ ፈቃድ እንዳልሆነ ልብ ይበሉ፡፡ ቃለመጠይቅ አድራጊው መኮንን ለዚህ አስፈላጊ የሆኑ ጠያቄዎችን የሚጠይቅዎት ሲሆን ለይቶ ለማመልከቻዎ አስፈላጊ ቢሆኑ እና ለሚኒስቴሩ ውሴኔ አስፈላጊ ቢሆኑ ጠለቅ ብሎ ሚኒስቴሩ ደርሶ ከስቴቱን (አየርላንድ) ውሰጥ እንዲቆዩ ፈቃድ መስጠት አለመስጠቱ ውሣኔ አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አይደለም፡፡ ነገር ገን በቃለመጠይቁ ወቅት እንደዚህ አይነት ነገር ከተነሳ በቃለመጠየቅ አድራጊው በፅሁፍ ይሰፍሩ እና በሀገር ውስጥ ስለመቆየት አለመቆየትዎ ፈቃድ ለመስጠት ሚኒስቴሩ ለሚሰጠው ውሣኔ ግምት ውስጥ እንዲገቡ ይደረጋሉ፡፡

### 13.2 በስቴቱ (አየርላንድ) ውስጥ ለመቆየት ወይም ላለመቆየት ሚኒስቴሩ ፈቃድ ለመስጠት ወይም ለመከልከል ምን አይነት መረጃ አስፈላጊ ነው?

13.2.1 ሚኒስቴሩ ለአለማቀፍ ጥበቃ ባቀረቡት ማመልከቻ ውስጥ የተካተተን አስፈላጊ መረጃና በመጀመሪያ ቃለመጠይቅዎ እንዲሁም በግል ያለማቀፍ ጥበቃ ቃለመጠይቅዎ ወቅት እርስዎ የገለፆቻ ነገሮች ጨምሮ ማንኛውንም አስፈላጊ መረጃ ግምት ውስጥ ያስገባል፡፡

13.2.2 ሚኒስቴሩ ቤተሰብዎንና የግል ሁኔታዎን እንዲሁም ለግልዎ እና ለቤተሰብዎ ህይወት ያልዎትን መብት እና ለሚከተሉት ትኩረት ይሰጣል፡-

(i) ከስቴቱ (አየርላንድ) ጋር ያልዎትን የግንኙነት፣ የሚኖር ከሆነ

(ii) ሰብአዊ ጉዳዮች፣

(iii) የእርስዎ ባህሪና ስነምግባር በአየርላንድ ውስጥና ከዚያ ውጪ (የወንጀል ፍርዶችን ጨምሮ)፣

(iv) ብሔራዊ ደህንነትና የህብረተሰቡ ሰላም አንጻር፣ እና

(v) ለብዙሀኑ መልካም የሆኑ ሌሎች ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች፡፡

13.2.3 ሚኒስቴሩ እርስዎ የጥገኝነት ፈቃድ ስለመከልከልዎ ላነሷቸው ማንኛቸውም ጉዳዮች ትኩረት ይሰጣል፡፡ (**አንቀፅ 2.7.1 ይመልከቱ**)

## 13.3 የመቆየት ፈቃድ ከተከለከልኩኝ ምን ይፈጠራል?

13.3.1 በአለማቀፍ ጥበቃ ላይ በተሰጥዎት የውሳኔ ሀሳብ ላይ ለአይፒኤቲ ይግባኝ ካላሉ እና ሚኒስቴሩ በሀገር ውስጥ እንዲቆዩ ካልፈቀደ ከዛ በኋላ በስቴቱ (አየርላንድ) ውስጥ መቆየት አይችሉም፡፡ የእርስዎ ቲአርሲ የማያገለግል ስለሆነ ወዲያውኑ ለአይፒኦ መመለስ ይኖርብዎታል፡፡

13.3.2 ወደ መጡበት ሀገር/ቀድመው ይኖሩበት የነበረው ሀገር በፈቃደኝነት የመመለስ አማራጭ ያለልዎት ሲሆን በፈቃደኝነት ስቴቱን (አየርላንድ) ለቀው ለመውጣት ከወሰኑ ለአይፒኦ እና ለአይኤንአይኤስ ማሳወቅ ይኖርብዎታል፡፡

13.3.3 ወደ መጡበት ሀገር/ቀድመው ይኖሩበት የነበረው ሀገር በፈቃደኝነት መመለስ ካልፈለጉ ሚኒስቴሩ ከአየርላንድ ለቀው ወደውጪ የትኛውም ሀገር እንድሄዱ አስገዳጅ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

## 13.4 የመቆየት ፈቃድ ከተሰጠኝ ምን ይፈጠራል?

13.4.1 የመቆየት ፈቃድ ከተሰጥዎት ምን ማድረግ እንዳለብዎትና ስለሙብትና ግዴታዎ ዝርዝር የያዘ ደብዳቤ ይደርስዎታል፡፡

## 13.5 የመቆየት ፈቃድ ክልከላ እንዴት «በድጋሚ ይታያል»?

13.5.1 እንዳይቆዩ በተሰጠው የፈቃድ ክልከላ ላይ ይግባኝ መጠየቅ አይችሉም፡፡

13.5.2 ከአለም አቀፍ ጥበቃ ጋር በተያያዘ አይፒኦ የውሣኔ ሀሳብ ከከለከልዎት እንዴት ለአይፒኤቲ ይግባኝ እንደሚያቀርቡ መረጃ ያገኛሉ፡፡ ለአይፒኤቲ ይግባኝ አቅርቦ እሱም የአይፒኦን አሉታዊ የውሣኔ ኃሳብ ካፀደቀ እንድትሞሉት *የመቆየት ፈቃድ ድጋሚ መከለሻቅፅ* የሰጥዎታል፡፡ ቅፁን ሞልተው ጨርሰው የሚመልሱበት ጊዜ ገደብ በቅፁ ላይ ሰፍሮ ይገኛል፡፡

13.5.3 ሚኒስቴሩ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲቆዩ ፈቃድ ከሰጥዎት ጊዜ ጀምሮ አይፒኤቲ ባቀረቡት ያለማቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ላይ ውሣኔ እስኪሰጥ ድረስ የእርስዎ ሁኔታ ከተለወጠ በማንኛውም ረገድ ለሚኒስቴሩ የመቆየት ውሣኔ አስፈላጊ እንደሆነ ወዲያውኑ እንዳወቁ ይህንኑ ለሚኒስቴሩ ማስረዳት ይኖርብዎታል፡፡

13.5.4 እርስዎ የሁኔታዎን መለወጥ በማመልከት ማንኛውንም ለሚኒስቴሩ የመቆየት ፈቃድ አስፈላጊ

የሆነ መረጃ ያቀረቡ እንደሆነ ሚኒስቴሩ የመቆየት ፈቃድ ክልከላ ውሣኔውን በድጋሚ የሚቀንስ ይሆናል፡፡ እንደዚሁም ሚኒስቴሩ ከላይ **በአንቀፅ 13.2.2** ስር ለተቀመጠውና እርስዎ ለሚያቀርቡት ተጨማሪ መረጃ ትኩረት ይሰጣል፡፡ ሚኒስቴሩ እንዲሁም ስለ ፈቃድ ክልከላው ያቀረቧቸውን ጉዳዮች ግምት ውስጥ ያስገባሉ፡፡

13.5.5 ሚኒስቴሩ የእርስዎን የመቆየት ፈቃድ ውሣኔ ከከለሰ በኋላ ለተወሰነ ጊዜ የሚቆይበትን የጊዜያዊ መቆያ ፈቃድ ሊሰጥዎ ወይም ሊከለክልዎ ይችላል፡፡ ለውሣኔው ምክንያት የሆነውን በማብራራት ሚኒስቴሩ ውሣኔውን በፅሁፍ የሚያሳውቅዎት ይሆናል፡፡

## 13.6 የመቆየት ፈቃድ ቢሰጠኝ እና በአይፒኦ በእኔ የጥበቃ ማመልከቻ ላይ በተሰጠው የውሣኔ ሀሳብ ላይ ለአይፒኤቲ ይግባኝ ብል ምን ይፈጠራል?

13.6.1 የእርስዎ በስቴቱን (አየርላንድ) ውስጥ የመቆየት ፈቃድ ተፈፃሚ እንዲሆን አሁንም በአካባቢዎ በሚገኝ የሚገኝ የፍልሰት ምዝገባ ፅ/ቤት መመዝገብ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን የጥበቃ ውሣኔው ላይ ይግባኝ ከጠየቁ አሁንም ድረስ ለአለማቀፍ ጥበቃ በአመልካችነት ደረጃ ስላሉ የአይፒኤቲ ውሣኔ እስኪታወቅ ድረስ በማንኛውም ስራ፣ ንግድ ወይመ ሙያ ላይ የመሰማራት ወይም የመቀጠር መብት የልዎትም፡፡

## 13.7 ጉዳዩ በድጋሚ ከታየ በኋላ ፈቃድ ከተከለከልኩ ምን ይፈጠራል?

13.7.1 የመቆየት ፈቃድ ተከልክለው ከሆነ በስቴቱን (አየርላንድ) ውስጥ ከዛ በኋላ መቆየት አይቻልም፡ ፡ የጊዜያዊ መኖሪያ ፈቃድዎ ከዛ በኋላ የማያገለግል ስለሆነ ወዲያውኑ ለአይፒኦ ይመልሱ፡፡

13.7.2 ወደ መጡበት ሀገር/ቀድመው ይኖሩበት የነበረው ሀገር በፈቃደኝነት የመመለስ አማራጭ ያልዎት ሲሆን በፈቃደኝነት ስቴቱን (አየርላንድ) ለቀው መውጣት ከፈለጉ ለአይፒኦ እና አይኤንአይኤስ ማሳወቅ ይኖርብዎታል፡፡

13.7.3 ወደ መጡበት ሀገር/ቀድመው ይኖሩበት የነበረው ሀገር ሀገር በፈቃደኝነት ላለመመለስ ከወሰኑ ስቴቱን (አየርላንድ) ለቀው እንዲወጡ እና ከስቴቱን (አየርላንድ) ውጪ የትም ቦታ እንዲቆዩ ሚኒስቴሩ አስገዳጅ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

## ክፍል 14
## የቤተሰብ መቀላቀል

### 14.1 የቤተሰብ ቅልቅል/እንደገና መገናኘት ምንድን ነው?

14.1.1 ሚኒስቴሩ የስደተኝነት መብት ወይም የንዑስ ጥበቃ ማረጋገጫ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ **የተወሰኑ** የቤተሰብዎ አባለት ፈቃድ አግኝተው

- በማመልከቻው ቀን ውጪ ሀገር ካሉ ወደ ስቴቱ (አየርላንድ) ገብተው እንዲኖሩ፣ ወይም

- በማመልከቻው ቀን ስቴቱ (አየርላንድ) ውስጥ የሚገኙ ከሆነ በስቴቱ (አየርላንድ) ውስጥ ቀርተው እንዲኖሩ እንዲፈቀድላቸው

ለሚኒስቴሩ ማመልከት ይኖርብዎታል፡፡

### 14.2 የጊዜ ገደብ ይኖራል?

14.2.1 ለቤተሰብዎ አባላት የስደተኝነት ወይም የንዑስ ጥበቃ ማረጋገጫ ከተሰጥዎት ቀን ጀምሮ **በ12 ወራት** ውስጥ ከእርስዎ ጋር እንዲቀላቀሉ ለቤተሰብዎ አባላት ማመልከቻ ማስገባት ይኖርብዎታል፡፡

### 14.3 የቤተሰብ አባል ማን ነው?

14.3.1 **የቤተሰብ አባል** በጥብቅ ፍቺ ይሰጠዋል፡፡ ይህም ማለት፡-

(i) በስቴቱ (አየርላንድ) ውስጥ የአለማቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ በቀረበበት ቀን ጋብቻው በፅናት ያለ ከሆነ የግለሰቡ ባል ወይም ሚስት ይህንን የሚያቀርቡ ከሆነ፣

(ii) በስቴቱ (አየርላንድ) ውስጥ የአለማቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ በቀረበበት ቀን ጓደኛ በፅናት ያለ ከሆነ የግለሰቡ ጓደኛ ይህንን የሚያቀርቡ ከሆነ፣

(iii) ግለሰቡ እድሜው ከ18 አመት በታች ከሆነና ያላገባ ከሆነ፣ የእርሱ/የእርሷ ወላጆችና ልጆቻቸው ከ18 በታች የሆናቸውና ያላገቡ፣ ወይም

(iv) የቤተሰብ ቅልቅል ማመልከቻው በቀረበበት ቀን እድሜው ወይም እድሜዋ ከ18 አመት በታች የሆነ እና ያላገባች የግለሰቡ ልጅ፡፡

### 14.4 በአለማቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ቅፅ እና መጠይቅ ውስጥ ምን ምን መረጃ ማካተት ይኖርብኛል?

14.4.1 ለአለማቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ሲያቀርቡ ምን አልባት እርስዎ የአለማቀፍ ጥበቃ ከተሰጥዎት ለቤተሰብ ቅልቅል ብቁ የሚሆኑ የቤተሰብ አባላትን አስፈላጊ መረጃ ማካተት ይኖርብዎታል፡፡ (**አንቀፅ 14.3**) ይመልከቱ፡፡

14.4.2 በአለማቀፍ ጥበቃ መጠይቅ ውስጥ ስለቤተሰቡ አባላት አስፈላጊ መረጃ ማካተት ይኖርብዎታል፡፡

14.4.3 የአለማቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ እና መጠይቅ በሚሞሉበት ጊዜ የቤተሰብዎን አባላት ዝርዝር መረጃ ማካተት እና እንደልደት ምስክር ወረቀት ጋብቻ ምስክር ወረቀት ወዘተ ያሉ አስፈላጊ ማስረጃዎችን ማቅረብ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

## 14.5 ለቤተሰብ ቅልቅል ማመልከቻ የማቀርበው እንዴት ነው?

14.5.1 የስደተኛ ወይም የንዑስ ጥበቃ ከተሰጥዎት እና የቤተሰብዎ አባላት ቅልቅል ማለትም **በአንቀፅ 14.3** ስር ለተጠቀሱት የቤተሰብ አባላት ማመልከቻ ማቅረብ ከፈለጉ በሚከተለው አድራሻ ማመልከቻዎን ለቤተሰብ ቅልቅል ቡድን /አይኤንአይኤስ/ በፅሁፍ ማቅረብ ይኖርብዎታ፡፡

**Family Reunification Unit**
**Irish Naturalisation and Immigration Service**
**13/14 Burgh Quay**
**Dublin 2**
**D02 XK70**

14.5.2 ለተጨማሪ መረጃ በ www.inis.gov.ie ላይ ይገኛል

**የቤተሰብ ቅልቅል ማመልከቻ የስደተኝነት መብት ወይም የንዑስ ጥበቃ ማረጋገጫ ከተሰጥዎት ጊዜ አንስቶ በ 12 ወራት ጊዜ ውስጥ መቅረብ እንዳለበት ያስታውሱ፡፡**

## ክፍል 15
## *መኖሪያዎች*

### 15.1 *የቅበላ/ የመኖሪያ ቦታ መረጃ*

15.1.1 ለአለማቀፍ ጥበቃ በአይፒኦ ካመለከቱ የመጀመሪያ ዝርዝሮችዎ መረጃዎች ተሰናድቶ ለአርአይኤ ማለትም መንግስት የሚያቀርበውን መኖሪያ በተመለከተ ሁሉን ነገር ለሚቆጣጠረው አካል ይላኩና ማረፊያ ይመቻችልዎታል፡፡

15.1.2 መኖሪያ ከፈለጉ የእርስዎ ዝርዝር መረጃ ገብቶ የሚኖሩበት ቤት ሊሰጥዎ ይችላል፡፡ የሚሰጥዎትን ቤት ከተቀበሉ፣ ወደ አጭር ግዜ ወደሚቆዩበት የመቀበያ ማእከል የሚወስዶት መጓጓዣ ይዘጋጅሎታል - ቆይታው ብዙ ግዜ ከሶስት ሳምንታት አይበልጥም፡፡

15.1.3 ለአጭር ጊዜ በቅበላ ማእከል ከቆዩ በኋላ ወደመኖሪያ ማእከል ይመራሉ፡፡ ስለሚዛወሩተብ ቦታ መገኛ ምንም አይነት ምርጫ አይሰጥዎትም፡፡

15.1.4 ወደ ተላኩበት የማረፊያ ማእከል የአለማቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዎ ሙሉ በሙሉ (ይግባኝን ካሎት እሱንም ጨምሮ) አስኪጠናቀቅ ድረስ እንዲቆዩ ይደረጋል፡፡ ወይም በራስዎ ወጪ የግል ቤት ተከራይተው የሚቆዩበት እንደአማራጭ ይያዛል፡፡

15.1.5 በራስዎ ካመቻቹ የት እንዳሉ እና የት እንደሚኖሩ ለአይፒኦ ማሳወቅ እንዳለብዎት ልብ ይበሉ፡፡

15.1.6 በቅበላ ማእከል እና በመኖሪያ ማእከል የሚቀርብልዎት የማረፊያ ቤት ሁል ጊዜም በማእከሉ ተፈፃሚነት ያለውን የቤቶች ደንብቦች ይኖራሉ፡፡

15.1.7 በአርአይኤ አማካኝነት ከተሰጥዎት መኖሪያ ቤት ወደ ሌላ ቦታ ለመዛወር ሊጠይቁ የሚችሉ ሲሆን ይህ ተፈፃሚ የሚሆነው ኤጀንሲው ሌላ አማራጭ ማረፊያ ሊያቀርብልዎት የሚችል ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡

15.1.8 ተጨማሪ መረጃ ከቅበላና ፍልሰት ኤጀንሲ በ www.ria.gov.ie ላይ ማግኘት ይችላሉ፡፡

ቅጥያ

## የማግኛ ዝርዝሮች

**ለጥበቃ ማመልከቻዎት ግንኙነት ያለው ስቴትና ሌሎች ድርጅቶች ሊያገኙ የሚችሉበት የማግኛ ዝርዝር፡-**

| ድርጅት | ተግባር |
|---|---|
| Irish Naturalisation and Immigration Service,<br>Department of Justice and Equality.<br>13 – 14 Burgh Quay,<br>Dublin 2.<br>D02 XK70<br><br>ስልክ:- +353 1 616 7700<br>ውስን-ጥሪ:-1890 551 500<br>ድረገጽ:- www.inis.gov.ie | የአየርላንድ ዜግነት መስጠትና ፍልሰት አገልግሎት (አይኤንአይኤስ) በፍትህና እኩልነት ሚኒስቴር ስር ጥገኝነት ጠያቂ፣ ፍልሰት (ቪዛን ጨምሮ) እና የዜግነት ጉዳዮች ላይ የአስተዳደር ስራዎችን በሀላፊነት የሚሰራ ነው፡፡ እንዲሁም አይኤንአይኤስ የመንግስት አስተዳደር በፍልሰትና ጥገኝነት ጉዳዮች ላይ ውጤታማ አገልግሎት በነዚህ አካባቢዎች ላይ እንዲኖር ይሰራል፡፡ |
| International Protection Office<br>Irish Naturalisation and Immigration Service,<br>79-83 Lower Mount Street,<br>Dublin 2.<br>D02 ND99<br><br>ስልክ:- +353 1 602 8000<br>ፋክስ:- + 353 1 602 8122<br>ኢሜል:-info@ipo.gov.ie<br>ድረገጽ:- www.ipo.gov.ie | የአለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ (አይፒኦ) ተግባር፣ በተለየ፣ ግለሰቡ ለስቴት (አየርላንድ) አለም አቀፍ ጥበቃ ብቁ ስለመሆኑ በአለም አቀፍ አዋጅ 2015 ድንጋጌ መሰረት ግብረ መልስ ይሰጣል፡፡ አመልካቾች ለአለም አቀፍ ጥበቃ ብቁ ካልሆኑ፣ አይፒኦ አመልከቻቹ/አመልካቿ ወደ መጡበት በግዳጅ ከመመልስና ከመሳሰሉት ነገሮች ይልቅ በስቴቱ (አየርላንድ) የመቆየቱን ነገር ሊያጤን ይችላል፡፡ |
| International Protection Appeals Tribunal<br>6/7 Hanover Street,<br>Dublin 2.<br>D02 W320<br><br>ስልክ:- +353 1 474 8400<br>ውስን-ጥሪ: 1890 210 458<br>ፋክስ:- +353 1 474 8410<br>ኢሜል:- info@protectionappeals.ie<br>ድረገጽ:-www.protectionappeals.ie | የአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ችሎት (አይፒኤቲ) ከአይፒኦ የተገኘውን አሉታዊ ግብረ መልስ ላይ ይግባኝ በመጠየቅ ላይ ይሰራል፡፡ ይግባኙ የሚካሄደው በአይፒኤቲ አባል ነው፡፡ |

| ድርጅት | ተግባር |
|---|---|
| Reception and Integration Agency.<br>P.O. Box 11487<br>Dublin 2.<br><br>ስልክ:- + 353 1 418 3200<br>ፋክስ:- +353 1 4183271<br>ኢሜል:-RIA_Inbox@justice.ie<br>ድረገጽ:- www.ria.gov.ie | ቅበላና መስተንግዶ ኤጀንሲ (አርአይኤ) ያለበት ሀላፊነት ለጥበቃ አመልካቾች የመኖሪያና የመሳሰሉ አገልግሎቶችን ማስተባበር ነው:: ለጥበቃ አመልከቻቾች የሚሰጡት እነዚህ አገልግሎቶች የሚያጠቃልሉት የመኖሪያ፣ የጤና ድጋፍ፣ ትምህርትና የደህንነትን ነው:: |
| United Nations High Commissioner for Refugees.<br>102 Pembroke Road,<br>Ballsbridge,<br>Dublin 4.<br>D04 E7N6<br><br>ስልክ:- 01 631 4510<br>ድረገጽ:-www.unhcr.org | የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር (ዩኤንኤችሲአር) የስደተኞችን ፍላጎቶች ለመሟላት በ 1951 የተቋቋመ ነው:: የዩኤንኤችሲአር ስራዎች የሚገለጹት በሰብኣዊነት፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ-ያልሆነ ፍቺ ላይ ነው:: ዋና ዋና ተግባራቱ ለስደተኞች አለም አቀፍ ጥበቃ መስጠት፣ በችግር ላይ ላሉ ቋሚ መፍቴዎችን መሻትና የቁሳቁስ ድጋፍ ማድረግ ነው:: ጥበቃው በግዳጅ መመለስን ማለትም፣ ስደተኛው ስቃይ ወዳለበት ሀገር በግዳጅ እንዲመለስ/እንድትመለስ ማድረግን ለመከላከል ነው:: በዩኤንኤችሲአር ለመጀመሪያና ይግባኝ ደረጃ ማመልከቻዎች አካሄድ አለው:: ዩኤንኤችሲአር ማንኛውም አይነት ቃለመጠይቅ ወይም ችሎት ላይ ሊገኝ ወይም በማንኛውም አይነት ማመልከቻ ላይ ጽሁፍ ሊያስገባ ይችላል:: |
| International Organisation for Migration.<br>116 Lower Baggot Street,<br>Dublin 2.<br>D02 R252<br><br>ነጻ ጥሪ:- 1800 406 406<br>ስልክ:- +353 1 676 0655<br>ኢሜል:- iomdublin@iom.int<br>ድረገጽ:- www.ireland.iom.int/ | አለም አቀፍ የስደተኞች ድርጅት (አይኦኤም) የአውሮፓ ኢኮኖሚክ ቦታ (ኢኢኤ) ያልሆኑና የጉዞ ሰነድ ሳይኖራቸው ወደሀገራቸው መመለስ የሚፈልጉ ጥገኝነት ጠያቂዎችና ህገወጥ ስደተኞች ምስጢራዊ ድጋፍ ይሰጣል:: |

| ድርጅት | ተግባር |
| --- | --- |
| Legal Aid Board (Smithfield).<br>48/49 North Brunswick Street,<br>Georges Lane,<br>Dublin 7.<br>D07 PE0C<br><br>ስልክ:- (01) 646 9600<br>ፋክስ:- (01) 671 0200<br>ኢሜል:-lawcentresmithfield@legalaidboard.ie<br><br>Legal Aid Board (Cork)<br>Popes Quay Law Centre,<br>North Quay House,<br>Popes Quay,<br>Cork<br>T23 TV0C<br><br>ስልክ:- + 353 21 455 16 86<br>ፋክስ:- +353 21 455 1690<br>ኢሜል:-lawcentrecorknorth@legalaidboard.ie<br><br>Galway Law Centre (Seville House)<br>Seville House<br>New Dock Road<br>Galway<br>H91 CKVO<br>ስልክ:- +353 91 562 480<br>ፋክስ:- +353 91 562 599<br>ኢሜል:- lawcentresevillehouse@legalaidboard.ie | የአየርላንድ የአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካቾች ለሲቪልና የህግ ድጋፍም ማመልከት የሚችሉና ለአለም አቀፍ ይግባኝ ችሎቶች የሚያስፈልግ ከሆነ፣ ለጥበቃ ማመልከቻዎትና ሌላ ማንኛውም ይግባኝ ላይ የምክር እርዳታን መጠየቅ ይቻላል፡ ፡ |
| Team for Separated Children Seeking Asylum,<br>TUSLA- Child and Family Agency<br>Sir Patrick Dun's Hospital,<br>Lower Grand Canal Street,<br>Dublin 2.<br>D02 P667<br><br>ስልክ:- +353 1 647 7000<br>ፋክስ:- +353 1 647 7008<br>ድረገጽ:- www.tusla.ie | ቱስላ - ልጆችና ቤተሰብ ኤጀንሲ ከወላጆቻቸው ለተለዩ የአለም አቀፍ ጥበቃ ለሚያስፈልጋቸው ልጆች ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ድጋፍ በማድረግ እንደ መኖሪያ፣ ህክምናና ባምበራዊ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት ይሰራል፡፡ |

| ድርጅት | ተግባር |
|---|---|
| The Irish Red Cross Society.<br>16 Merrion Square North,<br>Dublin 2.<br>D02 XF85<br><br>ስልክ: +353 1 642 4600<br>ፋክስ:- +353 1 661 4461<br>ኢሜል:- info@redcross.ie<br><br>http://www.redcross.ie | የአየርላንድ ቀይ መስቀል የድንገተኛ ግዜና ሰብአዊ ድጋፍ ለማድረግ በበጎ ፈቃደኞቹ አውታረ መረቡ አማካኝነት በሀገር ውስጥና በአለም አቀፍ ደረጃ ይንቀሳቀሳል፡፡ |